የሰዶም ንጉሥ ደርሶ በአብራም ፊት ሰገደ፤

ወይቤ እግዚእነ አብራም ጸግወነ ነፍሰ እለ ባላሕከ፤

ጌታችን አብራም ! ያዳንኸውን ሰው ስጠን አለ፤

ወምሕርካሁሰ ይኩን ለከ፤

ምርኮው ግን ላንቱ ይሁን፤

እስመ ኢይከውን ብሔር ዘእንበለ ነፍስ፤

ሀገር ያለ ሰው አይሆንም አይጸናምና ያዳንከውን ሰው ስጠን፤

፴፱፤ወይቤሎ አብራም ሎቱ አነሥእ እደውየ ወእሌዕል ውስተ ሰማይ ኀበ አምላክ ልዑል እምፈትል እስከ ቶታነ አሣዕን ጥቀ ከመ ኢይነሥእ እምኵሉ ዘዚአከ፤

አብራምም እሱን እንዲህ አለው እጄን ገናና ወደሆነ ፈጣሪዬ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ ካንተ ገንዘብ ሁሉ ከፈትል ጀምሮ እስከ ጫማ ማዘቢያ ድረስ እንዳልቀበል፤

ከመ ኢትበል በሀሌ አነ አብእልክዎ ለአብራም፤

አበዓልክዎ ለአብራም ይላል አብነት አብራምን እኔ አከበርኩት አገነንኩት እንዳትል፤

ዘእንበለ ዘበልዑ ዳዕሙ ደቂቅየ ወራዙት፤

እነዚያ ጐልማሶች ከበሉት በቀር የተበላ አይመለስ፤ የፈሰሰ አይታፈስ እንዲሉ፤

ወባሕቱ ይንሥኡ ዕደው እለ ሖሩ ምስሌየ አውናን ወኤስኪል ወመምሬ እሙንቱ ወይኩን መክፈልተ ለእሉ ዕደው፤

ከእኔ ጋራ አብረውኝ የዘመቱ አውናን ኤስኪል መምሬ እነዚህ ፈንታቸውን ይውሰዱ እንጅ፤ ከአንተ ገንዘብ ሁሉ ከፈትል ጀምሮ እስከ ጫማ ማዘቢያ ድረስ እንዳልቀበል እጄን ልዑል ወደ ሆነ ፈጣሪዬ ከፍ ከፍ አድርጌ እምላለሁ አለው፤

## ምዕራፍ ፲፱

፩፤ወእምድኅረዝ ነገር በራብዕ ዓመት ዘዝ ሱባዔ በሠርቀ ወርኀ ሣልስ ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ አብራም በሕልም፤

ከዚህም ነገር በኋላ በዚህ ሱባዔ ባራተኛው ዘመን

በሶስተኛው ወር በሰኔ የእግ ዚአብሔር ቃል በአብራም ዘንድ በሕልም መጣ ተነ ገረ፤

እንዘ ይብል ኢትፍራህ አብራም አነ ውእቱ ቃውምከ ይቤሎ፤
አብራም ዋስ ጠበቃህ አለ ቃህ እኔ ነኝ አትፍራ አለው፤

ወአስብከ ይፈደፍድ ጥቀ፤
እኔ የምሰጥህ ዋጋህ እጅግ ብዙ ነው፤ ወብዙኅ አስብከ በንቤየ ይላል አብነት፤

፪፤ወይቤ አብራም እግዚኦ ምንተ ትሁበኒ፤
አብራምም አቤቱ ምን ዋጋ ትሰጠኛለህ አለ፤

ወአንሰ አሐውር ዘእንበለ ውሉድ፤
እኔ ልጅ ሳልወልድ በሞት እሄድአለሁ፤

ወልደ ማሴቅ ወልደ አማቲየል፤
የማሴቅ ልጅ የአማቲየል ልጅ፤

ዘደማስቆስ ኤልኤዜር ውእቱ ይወርሰኒ፤
ደማስቆስም ይላል የኤልኤ ዜር ልጅ ደማስቆስ እርሱ ይወርሰኛል፤

ወሊተ ኢወሀብከኒ ዘርአ፤
ለኔ ልጅ አልሰጠኸኝም፤

ሀበኒ ዘርዐ ፤
ለኔ ልጅ ስጠኝ አለው፤

፫፤ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብ ራም ኢይወርሰከዝ
እግዚአብሔርም አብራምን ይህ አይወርስህም፤ አለው፤

ዘእንበለ ዘይወጽእ እምከርሥከ ውእቱ ይወርሰከ፤
ከአብራክህ ከሚወለደው በቀር ሌላ አይወርስህም እርሱ ይወ ርስሃል እንጅ አለው፤

፬፤ወአውጽኦ አፍኣ ሌሊተ እግዚ አብሔር ለአብራም ወይቤሎ ነጽር ውስተ ሰማይ፤
እግዚአብሔር አብራምን ሌሊት ከተራራ ላይ አውጥቶ ወደ ሰማይ ተመልከት አለው፤

ወኍልቍ ከዋክብተ እመ ትክል ኍልቆቶሙ ፤
መቁጠር ይቻልህ እንደሆነ ከዋክብትን ቍጠር አለው፤

ወነጸረ ሰማየ ወርአየ ከዋክብተ፤
ሰማይን አየ ከዋክብትንም አየ፤

ወይቤሎ ኢይክል ኍልቆቶሙ፣
መቁጠር አይቻለኝም አለው፤
ወይቤሎ ከመዝ ይከውን ዘርእከ፣
ልጅህ ፣ እንደዚህ ኮከብ ይበዛል፤
ወአምኖ ለእግዚአብሔር፤
እግዚአብሔርንም አመነው፤
ወተኆቈ ጽድቀ፣
ይኸውም ማመኑ ጽድቅ ሆኖ ተነገረለት(ተቆጠረለት)፤ አንድም ስለ ጽድቅ ተቈጠረለት፤

፳፩፤ወይቤሎ አነ እግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፃእኩከ እምነ ዑር ዘከላውዴዎን ፤

ከከላውዴዎን ውስጥ ካለች ከዑር ያወጣሁህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለው፤

ከመ አሀብከ ምድረ ከነናውያን ለእኂዝ ለዓለም፣
ልትይዛት ልትገዛት ለዘለዓለም ይዘሀት ለመኖር የከነናውያንን ምድር እሰጥህ ዘንድ፤

ወለከዊን ለከ አምላከ፤
ፈጣሪህ ልሆን፣
ወለዘርእከ እምድኅሬከ፣
ካንተም በኋላ ለልጆችህ አምላክ ፈጣሪ ልሆን፡፡

፳፪፤ወይቤ አብራም እግዚኦ እግዚኦ በምንት አአምር ከመ እወርሳ፤
አቤቱ አቤቱ እንድወርሳት በምን አውቃለሁ አለ፡፡

፳፫፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ንሣእ ሊተ ጣዕዋ ዘ፫ቱ ዓመት ወጠሊ ዘ፫ቱ ዓመት ወበግዓ ዘ፫ ዓመት፣
ሶስት ዓመት የሆነው ጥጃ፣ ሦስት ዓመት የሆነው ፍየል፣ ሦስት ዓመት የሆነው በግ አምጣ አለው፤
ወመንጢጠ ወርግበ፤
ዋኖስ፣ርግብ አምጣ አለው፡፡

፳፬፤ወነሥአ ዘንተ ኵሎ በመንፈቀ ወርኅ ፤
ይህንን ሁሉ በወር እኩሌታ አመጣ፤ ማለት በሰኔ እኩሌታ አመጣ፣
ወውእቱሰ ይነብር ኀበ ድርስ ዘመምሬ እንተ ይእቲ ቅሩበ ኬብሮን፤

እሱ ግን በኬብሮን አቅራቢያ በምትሆን በወይራው አጠገብ ከግራሩ ሥር ተቀምጦ ነበር።

፱፤ወሐነፀ ህየ ምሥዋዐ፤

በዚያም መሠዊያውን ሠራ፤

ወዘብሐ ዘንተ ኵሎ፤

ይኽንን ሁሉ አረደ፤

ወከዐወ ደሞሙ ውስተ ምሥዋዕ፤

ደማቸውን በመሠዊያው ላይ አፈሰሰ፤

ወነፈቆን እማእከል ፤

ከሁለት ከሁለት አደረጋቸው ከፈላቸው፤

ወአንበሮሙ አንጻራቲሆሙ በበገጾሙ፤

በየፊታቸው በአንጻር በአንጻር አኖራቸው

## ጉባዔ

ወአዕዋፈሰ ኢነተፈ፤

ኢመተረ ሲል ነው አዕዋፍን ግን ጨርሶም አልቈረጣቸውም፤

ወይወርዱ አዕዋፍ ውስተ ስፍሐ፤

አዕዋፍ ወደመሥዋዕቱ ይወርዱ ነበር፤

፲፤ወይከልዮሙ አብራም፤

አብራም ይከለክላቸው ነበር፤

ወኢየሐድግ አዕዋፍ ይልክፍዎን ይከልዖን ሲል ነው፤ መከልከሉን አይተውም ነበር።

፲፩፤ወኮነ ሶበ ዐረበ ፀሐይ፤

ፀሐይ በገባ ጊዜ እንዲህ ሆነ፤

ድንጋፄ ወድቀ ላዕለ አብራም፤

በአብራም ላይ እንቅልፍ መጣበት፤

ወናሁ ግርማ ዓቢይ ጽልመት ወድቀ ላዕሌሁ፤

እነሆ የሚያስፈራ ግርማ ሌሊት ጽኑ ጨለማ መጣበት።

፲፪፤ወተብህለ ለአብራም አእምሮ አእምር ከመ ፈላሴ ይከውን ዘርእከ ውስተ ምድረ ነኪር ፤

ይቤሎ ሲል ነው፤ በከነዓን ሀገር ልጆችህ መጻተኛ እንዲሆኑ ፈጽመህ እወቅ ተብሎ በአብራም ተነገረ፤

ወይቀንይዎሙ፤

እንዲገዟቸው፤

ወየሐምምዎሙ ፬ተ ፻ ዓመተ ፤

ዓራት መቶ ዘመን መከራ እንዲያፀኑባቸው ተነገረ ፤

ወለአሕዛብኒ እለ ይትቀነዩ ሎሙ አነ እፌትሕ ሎሙ፤

ቦሙ ሲል ነው ለሚገዙላ ቸው እስራኤል ወገኖች እፈ ርድላቸዋለሁ።

፲፫፤ወእምድኅረዝ ይወጽኡ እም ህየ ምስለ ብዙኅ ጥሪት፤

ከዚህ በኋላ ከብዙ ገንዘብ ጋር ከዚያ ይወጣሉ፤

ወአንተ ተሐውር ኀበ አበዊከ በሰላም፤

አንተ ግን አባቶችህ ወደኼ ዱበት ወደ መቃብር በፍቅር ትወርድአለህ፤

ወትትቀበር በርስእ ሠናይ ፤

በበጎ እርጅና ማለት ሳታጣ ትቀበራለህ ማለት ነው።

፲፬፤ወበትውልድ ራብዕ ይትመየጡ ዝየ፤

በአራተኛው ትውልድ ወደ ዚህ ይመለሳሉ፤

እስመ ኢተፈጸመ ኀጢአቶሙ ለአሞራውያን እስከ አመ ይእዜ፤

እስከ ዛሬም ድረስ አለመመ ለሳቸው የአሞራውያን ኃጢ አት ባይፈጸም ነው።

፲፭፤ወነቅሐ አብራም እምንዋሙ ወተንሥአ፤

አብራም ከእንቅልፋ ፈጥኖ ተነሣ፤

ወፀሐይ ዓረበ፤

ፀሐይ ገባ፤

ወነድ ኮነ ፤

እሳት ይነድ ጀመር ፤

ወናሁ ዕቶን ይጠይስ ወነበልባለ፤ እሳት ኃለፈ ማዕከለ ስፍሐት፤ ምድጃው እየጤሰ እሳቱ እየ ነደደ በምሥዋዑ ላይ እነሆ አለፈ።

፲፮፤ወበይእቲ ሌሊት ተካየደ ኪዳነ እግዚአብሔር ምስለ አብ ራም፤

በዚያችም ሌሊት እግዚአብ ሔር ከአብራም ጋር መሐላ ውን ተማማለ፤

እንዘ ይብል ለዘርእከ እሁባ ለዛቲ ምድር እምፈለገ ግብጽ እስከ ፈለግ ዓቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ፤

ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ ኤፍ ራጥስ እስከሚባለው ሰፊ ወንዝ ድረስ ለልጆችህ ይህ

ችን ሀገር እሰጣታለሁ ብሎ ተማማለ፤

ለቄኔውስ ወለዜቄኔዜውስ ወለቀድሞኔውስ ወለፌራዜውስ ወለፌኮሬውስ ወለኤዌውስ ወለአሞሬዎስ ወለከናኔዎስ ወለጌርጌሴዎስ ወለኢያሴውስ፣

የቄኔዎስንና የዜቄኔዜውስን፣ የቀድሞኔውስንና የፌራዜውስን፣ የፌራኮሬውስንና የኤዌውስን፣ የአሞሬዎስንና የከናኔዎስን፣ የጌርጌሴዎስንና የኤያሴውስን፣ የነዚህን ሁሉ አገር ለልጆችህ እሰጣ ለሁ ብሎ መሐላውን ተማ ማለ።

፲፯፤ወኃለፈ አብራም ወአዕረገ ስፍሐተ፣

አብራምም ሄዶ መሥዊያውን አዘጋጀ፣

ወአዕዋፈ ወመሥዋዕቶሙ ወሞ ዓሕቶሙ፤

አዕዋፍን መሥዋዕቱን ወይ ኑን አቀረበ፤

ወበልዖ እሳት፤

እሳቱ በላው።

፲፰፤ወበዛቲ ሌሊት ይቤሉ መላእክተ ገጽ ተካየድነ ኪዳነ ምስለ አብራም፤

በዚያች ሌሊት የአብራም ባለሟሎቹ መላእክት ከአብ ራም ጋር መሐላን ተማ ማልን አሉ፣

በከመ ኪዳን ዘተካየድነ በዛቲ ወርኅ ምስለ ኖኅ፤

በዚች ወር ከኖኅ ጋር እንደ ተማማልን ከአብራም ጋርም ተማማልን አሉ።

፲፱፤ወአብራም ሐደሳ ለበዓል ወለሥርዐት ሎቱ እስከ ለዓለም፤ አብራም በዓልን፣ ሥርዓትን ለዘለዓለም አደሳት አጸናት፤

ወተፈሥሐ አብራም ወአይድዓ ዘንተ ኵሎ ነገረ ለሶራ ብእሲቱ፤ አብራም ደስ ቢለው ይኸነን ሁሉ ነገር ለሶራ ሚስቱ ነገራት፤

ወአምነ ከመ ይከውኖ ዘርአ፣

ልጅ እንዲወለድለት አመነ፤

ወይእቲሰ ኢትወልድ፤

እርስዋ ግን ልጅ አትወል ድም ነበር፤

ወአምከረቶ ሶራ ለአብራም ምታ፤

ሶራ ባሏ አብራምን መከረ ችው፤

ወትቤሎ ባእ ኀበ አጋር ግብጻዊት፣

ከግብጽ ካመጣኋት አገልጋዬ አጋር ድረስባት አለችው፤
እስመ አሐዕን ለከ እምኔሃ ዘርአ፤

ከእሷ የተወለደውን ልጅ አሳ ድግልሃለሁና።

፳፤ወሰምዐ አብራም ቃለ ሶራ ብእሲቱ፤

አብራምም የሚስቱ የሶራን ቃል ሰማ፤

ወይቤላ ግበሪ፤

እንዳልሽ አድርጊ አላት፤

ወነሥአት ሶራ አጋርሃ ግብጻዊተ ተለአኪታ፤

የምታገለግላት ግብጻዊት አጋ ርን አመጣች፤

ወወሀበታ ለአብራም ምታ ከመ ትኩኖ ብእሲተ፤

ሚስት ትሆነው ዘንድ ለባሏ አብራም ሰጠቻት።

፳፩፤ወቦአ ኀቤሃ ወፀንሰት ወወለ ደት ወልደ ፤

ከሷ ዘንድ ደረሰ ፀነሰች ወንድ ልጅ ወለደች፤

ወፀውአ ስሞ እስማኤል፣

ስሙን እስማኤል አለው፤

በዓመት ሐምስ ዘዝ ሱባዔ ወበውእቱ ዓመት ፹ወ፮ ዓም በሕይወተ አብራም፣

አብራም በሕይወት በኖረ በሰማንያ ስድስት ዓመት በዚህ ዘመን ይኸ ሱባዔ በተ ጀመረ በሶስተኛው ዓመት።

፳፪፤ወበዓመት ሐምስ ዘሱባዔ ዘራብዑ ለኢዮቤልው ዝንቱ፣

በዚህ ኢዮቤልዩ በዐራተኛው ዘመን ባምስተኛው ሱባዔ ዓመት፤

በወርኀ ሣልስ በመንፈቀ ወርኀ ገብረ አብራም በዓለ ቀዳሚ ማዕረር ዘዘርዓ ሥርናየ፣

በሶስተኛው ወር በሰኔ እኩ ሌታ አብራም የዘራው የስን ዴው መከር ከመድረሱ አስ ቀድሞ በዐለ ሰዊትን አደረገ።

፳፫፤ወአዕረገ መሥዋዕተ ሐዲሰ ዲበ ምሥዋዕ ቀዳሚ እክል ለእግ ዚአብሔር፣

አዲሱን እህል ለእግዚአብ ሔር መሥዋዕት ሊሆን ከእ ህሉ አስቀድሞ የደረሰውን በመሠዊያው ላይ አቀረበ፤

ላሕመ ወበሐኩ፤ ወበግዐ ዲበ ምሥዋዕ ጽንሐሐ ለእግዚአ ብሔር፤

ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሚሆነውን ላሙን ሙክቱን በጉን በመሠዊያው ላይ አቀ ረበ፤

ወመሥዋዕቶሙ ወምግሕቶሙ ኵሎ አዕረገ ዲበ ምሥዋዕ ዘምስለ ስኂን፤

መሥዋዕታቸውን ወይናቸው ንም ይህን ሁሉ በመሠዊ ያው ላይ ከነጭ ዕጣን ጋር ለእግዚአብሔር አቀረበ።

፳፬፤ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ወይቤሎ ለአብራም፤

እግዚአብሔር አብራምን ታየው እንዲህም አለው፤

አነ አምላክ ሰደይ፤

እግዚአ ሲል ነው፤ ጌታ ፈጣሪ እኔ ነኝ፤ ዓረብ ያስዲ እንዲል፤

ወአሥምር በቅድሜየ ወኩን ፍጹመ፤

በፊቴ ተገዘር ፍጹም ሁን፤

ወእሁብ ኪዳንየ ማእከሌየ ወማዕከሌከ፤

በኔና በአንተ መካከል መሐላን አጸናሁ፤

ወአከብረከ ጥቀ፤

እጅግ አከብርሃለሁ።

፳፭፤ወወድቀ አብራም በገጹ፤

አብራምም በግንባሩ ፍግም ብሎ ወደቀ፤

ወተናገሮ እግዚአብሔር ወይቤ ናሁ ሥርዐትየ ምስሌከ፤

እግዚአብሔርም ተናገረው እነሆ ሥርዓቴ ከአንተ ጋራ ጸንታ ትኖራለች፤

ወእሬስየከ አበ ብዙኃን አሕዛብ፤

ለብዙ አሕዛብ አባት አደርግ ሀለሁ አለው።

፳፮፤ወኢይጸዋዕ እንከ ስምከ አብራም ፤

ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ አብራም አይባል ማለት አበ ውትዳን አይባል፤

ወይኩን ስምከ እምይእዜ ወእስከ ለዓለም አብርሃም፤

ከዛሬ ጀምሮ ለዘላለም ስምህ አብርሃም ይሁን እንጂ ፤

እስመ አበ ብዙኃን አሕዛብ ሤምኩከ፤

የብዙዎች አሕዛብ አባት አድርጌአለሁና፤

ወአዓብየከ ኪያከ ጥቀ፤

አንተን እጅግ አከብርሀአለሁ፤

ወእሁበከ ውስተ አሕዛብ፤

አሕዛብን እሰጥሀአለሁ፤

ወነገሥት ይወጽኡ እምኔከ፤

ነገሥታት ካንተ ይወለዳሉ።

፳፮፤ወእሁብ ኪዳንየ ማዕከሌየ ወማእከሌከ ወማእከለ ዘርዕከ እምድኅሬከ በትዝምዶሙ ለሥር ዓት ዘለዓለም ፤

በእኔና በአንተ መካከል መሐላየን አፀናለሁ ካንተም በኋላ ለዘመዶቻቸው ለዘለዓ ለም ሥርዐት ሊሆን በልጆ ችህም መካከል ቃል ኪዳን እሰጥሀአለሁ፤

ከመ እኩንከ አምላከ ወለዘርዕከ እምድኅሬከ ኀበ ፈለስከ ምድረ ከነአን ዘትኴንን ለዓለም፤

ፈጣሪ እሆንህ ዘንድ ካንተም በኋላ ለዘለዓለሙ በምትገዛት ተሰደህ ወደሄድክበት በከነአ ንም፤

ወእከውኖሙ አምላከሙ ለዘርዕከ፤

ለልጆችህ ፈጣሪያቸው አምላ ካቸው እሆናቸዋለሁ።

፳፯፤ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአ ብርሃም፤

እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው ፤

ወአንተኒ ዕቀብ ኪዳንየ፤

አንተም መሐላዬን ጠብቅ፤

አንተ ወዘርዕከ እምድኅሬከ ተከ ሰቡ ኵሎ ሮስክሙ፤

ተገዘሩ ሲል ነው፤ ካንተ በኋላ የሚነሱት ልጆችህን ወንድ ወንዱን ግረዙ፤

ወተገዘሩ ኵሎ ቍልፈተክሙ፤

የሰውነታችሁን ሰንኮፍ ተገ ረዙ፤

ወይከውን ትእምርተ ሥርዓትየ ዘለዓለም ማዕከሌየ ወማከሌ ክሙ፤

የሥርዓቱም ምልክት በኔና በእናንተ መካከል ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።

ወለትውልድ፣

ለልጅ ልጅ ዘመን።

፳፱፤እመ ሳምንት ዕለት ትገዝሩ ኵሎ ሮሰ በትዝምድክሙ ፤ በየወገናችሁ በስምንተኛው ቀን ወንድ ወንዱን ግረዙ፣

ወልደ ቤት ወዘበወርቅ ተሣየጥ ክሙ እምኵሉ ውሉደ ነኪር፣ ከልጆችህ ወገን ከአሕዛብም ወገን በወርቅ የገዛችሁትን ከቤት የተወለደም ቢኖር፤

ወዘአጥረይክሙ ዘኢኮነ እምዘርዕ ክሙ ግዝረተ ይትገዘሩ፣

ከልጆችህ ወገን ያልሆነ በወርቅ የገዛችሁት ቢሆን ግዝረትን ይገረዙ፤

ወልደ ቤትክ ፤

ከቤትህ የተወለደም ቢሆን፣

ወዘበወርቅ ተሣየጥክ፣

በወርቅ የገዛኸውም ቢሆን፤

ይትገዘሩ፣

ይገረዙ፤

፴፤ወይከውን ኪዳንየ ውስተ ሥጋክሙ ለሥርዓትየ ዘለዓለም፣

ለዘለዓለም ሥርዓት ሲሆን መሐላየ በሰውነታችሁ ጸንቶ ይኖራል፤

ወዘኢኮነ ግዙረ ኵሉ ሮስክሙ ወዘኢተግዝረ ሥጋ ቍልፈቱ በዕለት ሳምንት ትሴሮ ይእቲ ነፍስ እምዘመዳ፣

ግዙር ያልሆነ ወንድ ልጃችሁ ሁሉ በስምንተኛው ቀን አባለ ዘሩን ያልተገረ ዘውም እንዲህ ያለች ሰውነት ከወገኗ ትለያለች ትጠፋለች፣ ትጥፋ አለው፣

እስመ ኪዳንየ ነሠተ፤

መሐላየን አፍርሶአልና።

፴፩፤ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብ ርሃም ሶራ ብእሲትክ ኢትፀዋዕ እንክ ሶራ፣

እግዚአብሔርም አብርሃምን ከንግዲህ ወዲህ ሚስትህ ሶራ አትባል፣

ሶራ ማለት እመ ውትዳን ማለት ነውና ፤

እስመ ሳራ ስማ፣

እሳ ያለበት ነው፤

ስሟ ሳራ ይባል እንጂ፣

ሳራ ማለት እመ ብዙኃን

ማለት ነው፤

ወእባርከ

አከብራታለሁ፣

ወእሁበከ እምኔሃ ወልደ፤

ከርሷም ልጅ እሰጥሀለሁ፤

ወእባርኮ ወይከውን ሕዝበ ዓቢየ፣

አከብረዋለሁ፤ ደግ ወገን አደ ርገዋለሁ ፤

ወነገሥተ አሕዛብ እምኔሁ ይከ ውኑ።

የአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ ከሱ ይወለዳሉ አለው።

፴፪፤ ወወድቀ አብርሃም በገጹ፣

አብርሃም በፊቱ ፍግም ብሎ ወደቀ፤

ወተፈሥሐ ወይቤ፣

በልቡ ደስ አለው ፤ በልቡም እንዲህ አለ፤

እስመ በዘ፻ትኑ ዓመቱ ይወልድ ወልደ፤

እወልድ ሲል ነው በመቶ ዘመኔ ልጅ እወልድ አለሁን?

ወሳራሂ እንተ ፺ ዓመታ ትወልድ ወልደ ፤

ሳራስ ዘጠና ዓመት ከሆናት በኋላ ትወልዳለችን፤ አንተ በቸርነትህ እንደሆነ ነው እንጅ ብሎ ደስ አለው።

፴፫፤ ወይቤሎ አብርሃም ለእግዚአ ብሔር መፍትው ይሕየው እስማ ኤል ቅድሜከ፣

አብርሃምም እግዚአብሔርን እስማኤል በፊትህ ይኖር ዘንድ ይገባል አለው።

፴፬፤ ወይቤ እግዚአብሔር አዎ፣

እግዚአብሔርም እንዳልህ ይሁን አለው፣

ወሳራሂ ትወልድ ለከ ወልደ፣

ሳራም ወንድ ልጅ ትወልድ ልሃለች፤

ወትሜውእ ስሞ ይስሐቅ፣

ስሙንም ይስሐቅ ትለዋለህ፤

ወአቀውም ኪዳንየ ምስሌሁ ኪዳነ ዘለዓለም፣

ለዘለዓለም ሥርዐት ሊሆን መሐላየን ከሱ ጋራ አጸና ለሁ፣

ወለዘርዑ እስከ ለዓለም እም ድኅሬሁ፣

ከሱም በኋላ ለልጆቹ መሐላ
ዬን አጸናለሁ።

፳፡ወበእንተ እስማኤልሂ ሰማእ
ኩከ፤

ስለ እስማኤልም የለመን
ከውን ነገር ሰማሁህ ፤

ወናሁ እባርኮ ወአልህቆ ወአበ
ዝኆ ጥቀ፤

እነሆ ፈጽሜ አከብረዋለሁ
አገነዋለሁ እጅግም አበዛዋ
ለሁ፤

ወ፲ወ፪ተ መሳፍንተ ይወልድ፤

ዐስራ ሁለት መሳፍንትን ይወ
ልዳል፤

ወእሠይሞ ውስተ ሕዝብ ዓቢይ፤

በብዙ ወገን ላይ እሾመዋ
ለሁ።

፳፩፡ወኪዳንየሰ አቀውም ምስለ
ይስሐቅ ዘትወልድ ለከ ሳራ
ለዘከመዝ መዋዕል በዓመት
ካልዕ፤

መሐላዬን ግን በሁለተኛው
ዓመት በእንዲህ ያለ ወራት
ሳራ ከምትወልድልህ ከይስ
ሐቅ ጋራ አጸናለሁ፤

ወፈጺሞ እንዘ ይትናገር ምስሌሁ
ዐርገ እግዚአብሔር እመልዕልተ
አብርሃም፤

ከሱ ጋራ ይኸንን ተናግሮ
ከጨረሰ በኋላ እግዚአብሔር
አብርሃም ከአለበት ወደሰ
ማይ ወጣ።

፳፫፡ወገብረ አብርሃም በከመ
ይቤሎ እግዚአብሔር ፤

አብርሃምም እግዚአብሔር እን
ዳለው አደረገ፤

ወነሥአ እስማኤልሃ ወልዶ
ወኵሎ ልደ ቤቱ ወዘሂ ተሣየጠ
በወርቁ ኵሎ ሮሰ ዘውስተ ቤቱ
ወገዘረ ሥጋ ክስበቶሙ፤

ልጁ እስማኤልን ፤ ከቤቱ
የተወለደ ባሪያውን በወርቁ
የገዛውን በቤቱ ያለውን ወን
ዱን ሁሉ አምጥቶ የሰውነ
ታቸውን ሰንከፍ ቆርጦ ጣለ።

፳፮፡ወበጊዜ ዛቲ ዕለት ተገዝረ
አብርሃም ወሰብአ ቤቱ ወኵሎሙ
እለ በወርቅ ተሣየጠ፤

በዚያች ቀን አብርሃምና ቤተ
ሰቦቹ በወርቅ የገዛቸው ሁሉ
ተገረዙ፤

ወእምውሉድ ነኪራንኒ ተገዘሩ

ምስሌሁ ፤

ልዩ የሚሆኑ የአሕዛብ ልጆችም ከሱ ጋራ ተገረዙ፤

ወዛቲ ሕግ ትኩን ለኵሉ ትውልድ ዘለዓለም፤

ለዘለዓለም ለሚኖር ትውልድ ሁሉ ይህች ሥርዓት ትጽና።

፴፱፤ወአልቦ ክትረቲ መዋዕል፤

ወሰነ መዋዕል ሲል ነው ፍጻሜ የለውም፤

ወአልቦ ተዐድዎ አሐተ ዕለተ እምሰሙን መዋዕል፤

ከሳምንቱ አንዲት ቀን መተላለፍ የለም፤

እስመ ሥርዓት ዘለዓለም ውእቱ፤

የዘለዓለም ሥርዓት ነውና፤

ወዝንቱ ሥሩዕ ወጽሑፍ ውስተ ጽላተ ሰማይ፤

ይህም በመላእክት ልቡና ተጽፏል ታዟል።

፵፤ወኵሉ ዘኢተገዝረ ሥጋ ነፍስቱ እስከ ሰሙን ዕለት፤

እስከ ስምንት ቀን ድረስ የሰውነቱን ሰንከፍ ቆርጦ ያልጣለ፤

ኢኮነ እምውሉደ ሥርዓት ዘተካየደ እግዚአብሔር ለአብርሃም ፤ እግዚአብሔር አብርሃምን ከተማማለው ሥርዓት ልጆች አይደለም፤

እስመ እምውሉደ ሙስና ውእቱ፤

ጥፋት ከሚስማማቸው ወገን ከአሕዛብ ነውና ነው።

፵፩፤ወአልቦ እንከ ትእምርት ላዕሌሁ ከመ ይኩን ለእግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔር ወገን ይሆን ዘንድ ምልክት የለውም ፤ እስመ ለአማስኖ ወለተንኩሎ እምነ ምድር ወለተሠርዎ እምነ ምድር፤

ከዚህ ዓለም ለመነቀል ከዚህ ዓለምም ፈጽሞ ለመጥፋት ተዘጋጅቷልና፤

እስመ ኪዳኖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ነሠተ፤

የፈጣሪያችን የእግዚአብሔርን ሥርዓት አፍርሷልና፤

እስመ ኵሎሙ መላእክተ ገጽ፤

ባለሟልነት ያላቸው መላእክት ግዙራነ ልብ ናቸውና፤

ወኵሎሙ መላእክተ ቅዳሴ ከመዝ ፍጥረቶሙ እምዕለተ ተፈጥሩ፤

ለምስጋና የተፈጠሩ አለቆች ሁሉ ከተፈጠሩበት ቀን ጀምሮ ተፈጥሮአቸው እንደ ዚህ ነውና፤

፴፪፤ ወእንዓርሙ ለመላእክተ ገጽ ወለመላእክተ ቅዳሴ ፤ በማያመሰግኑና ባለሚልነት ባላቸው መላእክት አንዓር ከእሱ ጋር ይኖር ዘንድ፣

ቀደሶ ለእስራኤል ከመ ይኩኑ ምስሌሁ ወምስለ መላእክቲሁ ቅዱሳን፣

ንጹሐን ከሆኑ ከመላእክትና ከሱ ጋር ይኖር ዘንድ እስ ራኤልን መረጠው፤

፴፫፤ወእንተኒ አዝዝ ለውሉደ እሰራኤል፤

አንተ የእስራኤልን ልጆች እዘዝ፤

ወይዕቀቡ ትእምርተ ዝ ኪዳን፤

የዚህን መሐላ ምልክት ይጠ ብቁ ዘንድ፤

ወለትውልዶሙ ለሥርዓት ዘለዓ ለም፤

ለልጆቻቸው ለዘለዓለም ሥር ዐት ሲሆን፣

ወኢይሠረዉ እምነ ምድር ፤

ከዚህ ዓለም እንዳይጠፉ፤

እስመ ትእዛዝ ተሠርዐ ለኪዳን ከመ ይዕቀብዎ ለዓለም ዲበ ኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል፣

በእስራኤል ልጆች ሁሉ ላይ ይጠብቁት ዘንድ ትእዛዝ ለመሐላ ተሠርቷልና፤

እስመ እስማኤልሃ ወውሉዶ ወአኀዊሁ ወኤሳውሃ ኢያቅረበ ኀቤሁ እግዚአብሔር፤

እስማኤልን ልጆቹን፤ የወን ድሞቹን ልጆች፣ኤሳውን እግ ዚአብሔር ወደሱ ባለሚልነት አላቀረበምና፤

ወኢኀረየ ቦሙ እስመ ውሉደ አብርሃም እሙንቱ፣

ምንም የአብርሃም ልጆች ቢሆኑ እነርሳቸውን አልመረ ጠምና፣

እስመ አእመሮሙ ፤

ክፉ እንደሆኑ ያውቃልና፣

፴፩፤ወእስራኤልሃ ኃረየ ይኩንዎ ሕዝበ ወቀደሶ፤

ወገን ይሆነው ዘንድ፣ እስራኤልን መረጠው አከበረው፣

ወአስተጋብኦ እምኵሉ ውሉደ ሰብእ፣

ከብዙ ሰው ለይቶ ሰበሰበው፣

እስመ ብዙኀ አሕዛብ ወብዙኀ ሕዝብ ወኵሉ ሎቱ፣

ብዙ አሕዛብ ብዙ ሕዝብ ሁሉም የሱ ወገኖች ናቸውና፣

ወዲበ ኵሉ አስለጠ መናፍስተ ከመ ያስሕትዎሙ እምድኅሬሁ፤

ከሱ በኋላ ያስቷቸው ዘንድ አጋንንትን በሰው ላይ አሰለጠነበት አሰናበተበት፤

፴፪፤ወዲበ እስራኤልሰ ኢያሥለጠ ወኢመነሂ መልአከ ወመንፈሰ፣

በእስራኤል ላይ ግን ማንንም ማን መልአክንም ቢሆን ሰይጣንንም ቢሆን አላሰለጠነም፣

እስመ ውእቱ ባሕቲቱ መኰንኖሙ፣

ገዥአቸው እሱ ብቻ ነውና፣

ወውእቱ የዐቅቦሙ፣

እሱ ይጠብቃቸዋል፤

ወይትኃሠሦሙ፤

እምእደ መላእክቲሁ ወእምነ መናፍስቲሁ፤

ከመላእክት እጅ ከአጋንንትም ይመራመራቸዋል፤

ወእምእ ደኵሎሙ ትእዛዛቲሁ ከመ ይዕቀቡ፣

ትእዛዙን ይጠብቁ ዘንድ ከሁሉም እጅ ይመራመራቸዋል።

ወይባርኮሙ ይኩንዎ ሎቱ ውሉዶ፤

ልጆቹ ይሆኑ ዘንድ ያከብራቸዋል፣

ወውእቱ ይኩኖሙ ሎሙ እምይእዜ ወእስከ ለዓለም፣

ከዛሬ ጀምሮ ለዘለዓለሙ ፈጣሪ ይሆናቸው ዘንድ ።

፴፫፤ወይእዜኒ እዜንወከ ከመ በዛቲ ሥርዐት ይሔስዉ ውሉደ እስራኤል፣

አሁንም የእስራኤል ልጆች ይህችን ሥርዓት እንዳፈረሱ እኔ እነግርሀለሁ፣

ወኢይገዝሩ ውሉዶሙ በከመ ኩሉ ዝሕግ፤

እንደዚህ ሥርዐት ልጆቻቸ ውን አይገዝሩም፤

እስመ እምሥጋ ግዝረቶሙ ይከውኑ መትርፋነ ውስተ ግዝረተ ውሉዶሙ፤

በሥጋቸው ከመገዘራቸው የተ ነሣ ልጆቻቸውን ሳይገዝሩ ይቀራሉ፤

ወኵሎሙ ውሉደ ቤልሆር የሐድጉ ውሉዶሙ ዘእንበለ ግዝ ረት በከመ ተወልዱ፤

የሰይጣን የቤልሆር ልጆች ሁሉ ልጆቻቸውን ሳይገዝሩ ይቀራሉ ይተዋሉ፤

፴፯፤ ወትከውን መዓት ዲበ ውሉደ እስራኤል ዓባይ እምነበ እግዚአብሔር፤

ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዞ በእስራኤል ልጆች ላይ ጽኑ መዓት ትሆናለች፤

እስመ ኀደጉ ኪዳኖ ፤

መሐላውን አፍርሰዋልና፤

ወእምቃሉ ተግኅሡ፤

ከሕጉም ርቀዋልና፤

ወወሐኩ ወጸረፉ በከመ ሥርዓቶ ኢገብሩ ለዝ ትእምርት፤

የዚህን ምልክት ሥርዓቱን እንዳላደረጉ መጠን ቅስፈቶ ቢል ቅስፈን ቅስፈን እያሉ አነሳስተውታልና፤

እስመ ገብሩ ነፍሳቲሆሙ ከመ አሕዛብ ለሰስሎ ወለተሠርዎ እምድር፤

ከዚህ ዓለም ለመጥፋት ለመ ራቅ ሰውነታቸውን እንደአ ሕዛብ አድርገዋልና።

፴፰፤ወአልቦ እንከ ሎሙ ኅድገት ወሥርየት፤

እንግዲህ ሥርየት ኅድገት የላቸውም፤

ከመ ይሠረይ ወይትኀደግ እም ኵሉ ኃጢአት ለስሕተተ ዛቲ ዓለም፤

በዚች ዓለም ስለሚሠራው ስሕተት ፈጽሞ ከኃጢአት ሁሉ ይርቅ ዘንድ።

፴፱፤ወበሠርቀ ወርኅ ራብዕ አስተርአይናሁ ለአብርሃም በኅበ ድርስ ዘማምሬም፤

ባራተኛው ወር በሐምሌ መባቻ በግራሩ አንፃር ባለ በወይራው ሥር ለአብርሃም ታየነው፤

ወተናገርነ ምስሌሁ፤

ከሱ ጋራ ተነጋገርን ፤

ወንሕነ አይዳእናሁ ከመ ሎቱ ይትወሀቦ ወልድ እምነ ሳራ ብእሲቱ፤

ከሚስቱ ሳራ ወንድ ልጅ እንዲሰጠው እኛ ነገርነው።

ወሰሐቀት ሳራ እስመ ሰምዓት ከመ ተናገርነ ዘንተ ቃለ ምስለ አብርሃም ፤

ከአብርሃም ጋራ ይህንን ነገር ስንነጋገር ሰምታለችና ሳራ ሳቀች፤

ወዘለፍናሃ ወፈርሃት፤

ገሠፅናት ፈራች፤

ወሐሰወት ከመ ስሕተት በእንተ ቃል፤

እንደ ሳቀች የተናገርነውን ቃል ሐሰት አደረገች።

፶፤ ወነገርናሃ ስሞ ለወልዳ በከመ ሥሩዕ ወጽሑፍ በስሙ ውስተ ጽላተ ሰማይ፤

ይስሐቅ በመላእክት ልቡና ስሙ ይስሐቅ ተብሎ እንደ ተጻፈ እንደታዘዘ የልጇን ስም ነገርናት፤

ወአመ ገባእነ ኀቤሃ በጊዜ ሰዓት፤

በጊዜው ጊዜ ወደሷ በተመለስን ጊዜ፤

ወይእቲኒ ፀንሰት ወልደ፤

እርሷም ወንድ ልጅን ፀነሰች።

፶፩፤ ወበዝ ወርኀ ገብረ እግዚአብሔር ኩነኔሆሙ ለሰዶም ወለገሞራ ወለሳቦዒም፤

በዚህ ወር እግዚአብሔር፤

የሰዶም የገሞራ የሳቦዒምንም ፍርዱን አደረገ፤

ወበኵሉ አድያመ ዮርዳኖስ፤

የዮርዳኖስን አውራጃ ሁሉ፤

ወአውዐዮሙ በእሳት ወበተይ፤

በእሳት በድኝ አቃጠላቸው፤ ወአጥፍኦሙ እስከ ዛቲ ዕለት፤ እስከዚች ቀን ድረስ አጠፋቸው፤

በከመ ናሁ አይዳዕኩክ ኵሉ ምግባሮሙ ከመ ፀዋጋን ወኃጥአን ጥቀ፤

ምግባራቸው ሁሉ እጅግ ክፉዎች ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ እንደሆኑ አሁን እንደ

ነገርሁሁ፣

ወይትራኩሱ ወይዜምዉ በሥጋሆሙ፣

በሰውነታቸው ይሰስናሉ የማይገባ ሥራ ይሠራሉ ፣

ወይገብሩ ርኵሰ በዲበ ምድር፣

በምድር ላይ የሚያፀይፍ ሥራን ይሠራሉ።

፶፪ ፣ ወከማሁ ይገብር እግዚአብሔር ኵነኔ በመካናቲሆሙ በውዕደ ይገብሩ በከመ ርኵሶሙ በሰዶም ከመ ኵነኔሃ ለሰዶም ፣

እንደ ሰዶም እንደገሞራ ያለ ኃጢአት በሠሩበት ሀገር እግዚአብሔር እንዲህ ይፈርዳል።

፶፫ ፣ ወለሉጥ አድኃኖ፣

ሉጥን አዳነው፣

እስመ ተዘከሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣

እግዚአብሔር አብርሃምን በረድኤት አስቦታልና ፣

ወአውጽኦ ለሉጥ እማእከለ ግፍታኤ፣

ሉጥን በሰዶም ከታዘዘው መከራ አወጣው፣

ወገብረ ውእቱኒ ወአዋልዲሁኒ ኃጢአተ በዲበ ምድር ፣

እሱም ልጆቹም በዚህ ዓለም ኃጢአትን ሠሩ፣

ዘኢኮነ ዲበ ምድር እመዋዕለ አዳም እስከኔሁ፣

ከአዳም ጀምሮ እስከዚያ ድረስ በምድር ተሠርቶ የማያውቅ፣

እስመ ሰከበ ብእሲ ምስለ ወለቱ፣

ሉጥ ከልጁ ደርሷልና።

፶፬፣ ወናሁ ተአዘዘ ወተቀርጸ ላዕለ ኵሉ ዘርዕ ውስተ ጽላተ ሰማይ፣

በልጆቹ ሁሉ ላይ ዕዳ መሆኑ በመላእክት ልቡና እንሆ ታውቋል ተቀርጿል፣

ከመ ያእትቶሙ ወከመ ይሥርዎሙ ፣

ፈጽሞ ያጠፋቸው ዘንድ፣

ወከመ ይግበር ኵነኔሆሙ ከመ ኵነኔ ሰዶም ፣

ፍርዳቸውን በሰዶም እንደፈረደ ይፈርድባቸው ዘንድ፣

ወከመ ኢያትርፍ ሉቱ ኵሉ

ዘርዐ ውስተ ምድር ዘሰብእ በዕለተ ደይን፤

ቊርጥ ፍርድ በሚፈርድባት ቀን የሰውን ዘር ሁሉ በዚህ ዓለም እንዳያስቀርበት እነሆ ታዘዘ፤

፶፭፤ወበዝ ወርኅ ግዕዘ አብርሃም እምኬብሮን ወሖረ ወኀደረ ማዕከለ ቃዴስ ወሱር ውስተ አድባረ ጌራሮን፤

በዚህ ወር አብርሃም ከኬብሮን ተነሥቶ በቃዴስና በሱር መካከል ወደ ጌራሮን ተራራ ሂዶ ኖረ።

፶፮፤ወበመንፈቀ ወርኅ ሐምስ ግዕዘ እምህየ ወኀደረ ኀበ አዘቅተ መሐላ፤

በአምስተኛ ወር በነሐሴ እኩሌታ ከዚያ ተነስቶ መሐላው በተደረገበት ቤርሳቤህ አደረ።

ምዕራፍ ፲፫

፩፤ወበመንፈቀ ወርኅ ሳድስ ሐወፃ እግዚአብሔር ለሳራ ፤ በስድስተኛው ወር በመስከረም እኩሌታ እግዚአብሔር ሳራን በረድኤት ጎበኛት፤

ወገብረ ላቲ በከመ ይቤ፤ እንደተናገረውም አደረገላት፤

ወፀንሰት ወወለደት ወልደ በወርኀ ሣልስ ወበመንፈቀ ወርኅ፤ በሦስተኛው ወር በሰኔ እኩሌታ ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤

በመዋዕል ዘይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም በበዓለ ቀዳሜ ማዕረር ተወልደ ይስሐቅ፤

እግዚአብሔር ለአብርሃም በነገረበት ቀን ከመኸሩ አስቀድሞ በሚሆን በበዐለ ሰዊት ይስሐቅ ተወለደ።

፪፤ወገዘሮ አመ ሳምንት ዕለት አብርሃም ለወልዱ፤

አብርሃም በስምንተኛይቱ ቀን ልጁን ይስሐቅን ገረዘው፤

ውእቱ ቀዳሚ ተገዝረ በኪዳን በከመ ተሠርዐ ለዓለም ፤ ለዘላለሙ ሥርዓት እንደ ታዘዘ አስቀድሞ እሱ በመሐላው ተገረዘ።

፫፤ወበዓመት ሳድስ ዘሱባዔ ራብዕ መጻእነ ኀበ አብርሃም ኀበ አዘቅተ መሐላ ፤

ባራተኛው ሱባዔ በስድስ

ተኛው ዓመት አብርሃም ወዳለበት ቤርሳቤህ መጣን፣

ወአስተርአይናሁ በከመ ንቤላ ለሳራ ከመ ንግባእ ኀቤሃ፣

ወደርሷ እንመለስ ዘንድ እንደነገርናት ታየነው፣

ወይእቲኒ ፀንሰት ወልደ፣

ይችውም ወንድ ልጅ ፀነ ሰች፡፡

፬፣ወተመየጥነ በወርኀ ሳብዕ ወረ ከብናሃ ለሳራ ዕንስተ ቅድሜነ፣ በሰባተኛው ወር ተመልሰን ሳራን በፊታችን ፀንሳ አገኘ ናት፣

ወባረክናሃ ለሳራ ወዜነውናሃ ኵሎ ዘተአዘዘ ሎቱ ከመ ኢይመ ውት ዓዲ እስከ ይወልድ ፮ ውሉደ፣

ሰባት ልጅ እኪወልድ ድረስ ዳግመኛ እንዳይሞት የታዘዘ ለትን ነገርናት ሳራንም አከበ ርናት፣

ወይሬኢ ዘርዐ ዘእንበለ ይሙት፣

ሳይሞት ዘርን እንዲያይ፡፡

፯፣ወበይስሐቅ ይጼዋዕ ሎቱ ስሙ ወዘርዑ፣

ስሙና ዘሩ በይስሐቅ ሲጠራ ይኖራል፣

ወኵሉ ዘርዐ ውሉዱ አሕዛበ ይከውኑ ፣

የልጅ ልጆቹ ብዙ ይሆናሉ፣

ወምስለ አሕዛብ ይትኌለቁ፣

ከአሕዛብም ጋራ ይቆጠራሉ፡፡

፯፣ወእምነ ውሉደ ይስሐቅሂ አሐዱ ይከውን ለዘርዕ ቅዱስ፣ ከይስሐቅ ልጆችም አንዱ ልዩ ወገን ይሆናል፣

ወውስተ አሕዛብ ኢይትኌለቁ ከአሕዛብ ጋራም አይቆጠርም፣

እስመ መክፈልተ ልዑል ይከ ውን፣

የልዑል እግዚአብሔር ዕድል ፈንታ ይሆናልና፡፡

<u>ጉባኤ</u>

፯፣ወውስተ ዘያመልኮ አምላክ ወረደ ኵሉ ዘርዑ ፣

ይስሐቅ ወደሚያመልከው አምላክ ዕድልነት ልጁ ሁሉ መጣ ፣

ከመ ይኩን ለእግዚአብሔር ሕዝበ ትርሲት እምኵሉ ሕዝብ፣

ለእግዚአብሔር ጌጥ ያለው ወገን ይሆን ዘንድ፣

ወከመ ይኩን ለመንግሥት ወለክህነት ወለሕዝብ ቅዱስ ፣ ነገሥታት ካህናት ከሱ ይወለዱ ዘንድ ክቡር ልዩ ወገንነት ያለው ይሆን ዘንድ።

፰፤ወሖርን ፍኖተነ ወዜነውናሃ ለሳራ ኵሎ ዘነገርናሁ ለአብርሃም፣

ለአብርሃም የነገርነውን ሁሉ ጎዳናችንን ሄደን ለሳራ ነገርናት፣

ወተፈሥሑ ፪ሆሙ ኅቡረ ፍሥሐ ዓቢየ ጥቀ፣

ሁለቱም አንድ ሁነው እጅግ ደስ አላቸው።

፱፤ወሐነፀ ህየ ምሥዋዐ አብርሃም ለእግዚአብሔር ዘባልሖ ወለዘአስተፍሥሖ በምድረ ኵሉ ፍልሰቱ፣

ተሰዶ በሄደበት አገር ሁሉ ደስ ለሚያሰኘው ለአዳነው እግዚአብሔር መሠዊያውን ሠራ።

፲፤ወገብረ በዓለ ፍሥሓ በዝ ወርኅ ሰቡዐ መዋዕለ በቅሩበ ምሥዋዕ ዘሐነፀ ኀበ አዘቅተ መሐላ፤

በቤርሳቤህ ባነፀው መሠዊያ አቅራቢያ በዚህ ወር ሰባት ቀን ደስ የሚያሰኝ በዓል አደረገ።

፲፩፤ወሐነፀ ምጽላላተ ሎቱ ወለአግብርቲሁ በዛቲ በዓል ፤

በዚች በዓል ለሱም ለልጆቹም ድንኳን ተከለ፤

ወውእቱ መቅድመ ገብረ በዓለ መጸለት በዲበ ምድር፤

እሱም አስቀድሞ በዚች ዓለም በዓለ መጸለትን አደረገ።

፲፪፤ወበገዝ ሰቡዕ መዋዕል ሀሎ ያቄርብ ኵሎ ዕለተ በበዕለት ውስተ ምሥዋዕ ጽንሐሐ ለእግዚአብሔር፤

በዚህ በሰባቱ ቀን ዕለት ዕለት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሚሆነውን ወደ መሠዊያው ያቀርብ ነበር ፣ አልሕምተ ፪ተ ወአባሕኰ ፪ተ፤

ሁለት ላም ሁለት ሙክት

ወአባግዓ ፯ተ፣

ሰባት በግ፣ እነዚህን አቀረበ፣

ወመሐስአ ጠሊ ፩ደ በእንተ ኃጢአት ከመ ያስተሥሪ ቦቱ በእንቲአሁ ወበእንተ ዘርዑ፣

ስለ እሱ ስለ ልጆቹ ያስተሠርይ ዘንድ ስለ ኃጢአት አንድ የፍየል ጠቦት አቀረበ።

፲፫፣ወለመሥዋዕተ መድኃኒት አባሕኰ ፯ተ ወመሐስዓ ጠሊ ፯ተ ወአባግዐ ፯ተ ወዳቤላተ ፯ተ፣

እንድንበትአለን ብለው ስለ ሚሰጡት መሥዋዕት ሰባት የበግ አውራ፣ ሰባት የፍየል ጠቦት፣ሰባት የበግ ሙክት፣ ሰባት የፍየል ሙክት ሠዋ፣

ወመሥዋዕቶሙኒ ወሞዓሕቶሙኒ ላዕለ ኵሉ ስብሐሙ የአጥን በዲበ ምሥዋዕ፣

መሥዋዕታቸውን ወይናቸውን በስቡ ላይ በመሠዊያው ያጥን፣ ነበር

ወያቄርብ ጽንሐሐ ኅሩየ ለመዓዛ ሠናይ፣

እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው የተመረጠውን መሥዋዕት አቀረበ።

፲፬፣በጽባሕኒ ወበሠርክኒ የአጥን አፈወ፣

ማታም ጧትም ሽቱውን ያጥን ነበር፣ አፈወ ያለው የወል ነው፣

ወስኂን፣

ነጭ ዕጣን፣

ወቀንዓተ ሚአ ወማየ ልብን፣

ልባንጃ ሽቱ፣

ወናርዶስ፣

ናርዶስ የሚባል ሽቱ፣

ወከርቤ፣

ከርቤ የሚባል ሽቱ፣

ወሰንበልተ

ሰንቡል፣

ወቍስጠ፣

ቀበርቾ፣

፯ቲሆሙ ዘንተ ኵሎ ያቄርብ፣

እነዚህን ሰባቱን ሁሉ ያቀርብ ነበር፣

ወውጉዓ፣

ጽሩየ ሲል ነው።

የተከለሰውንና፣

ወእዩነ

የተለቀመውን፣

ወዕሩየ ተአርዮ፣

በሚዛን የተካከለውንና፣

ወድሙረ፣

አንድ የሆነውን ፣

ወንጹሐ፣

የጠራውን ያቀርብ ነበር።

፲፩፣ወገብረ ዘንተ በዐለ ሰቡዓ መዋዕለ እንዘ ይትፌሣሕ በኵሉ ልቡ ወበኵሉ ነፍሱ፣

በፍጹም ሰውነቱ፣ በፍጹም ልቡናው ደስ እያለው ሰባት ቀን ይህን በዓል አደረገ፣

ውእቱ ወኵሎሙ እለ ውስተ ቤቱ፣

እሱ በቤቱ ያሉ ሁሉ በዓ ልን አደረጉ፣

ወአልቦ መኑሂ ነኪር ምስሌሁ፣

ከሱ ጋራ ባዕድ አልነበረም፣

ወኵሉ ዘኢኮነ ክሱበ፣

ግዙረ ሲል ነው ፣

ያልተገረዘ ሁሉ ከሱ ጋር አልነበረም።

፲፪፣ወባረከ አብርሃም ለፈጣሪሁ ዘፈጠሮ በትዝምዱ፣

አብርሃምም አዳምን የፈጠረ ጌታን አመሰገነው፣

እስመ ለሥምረቱ ፈጠሮ፣

ፈቃዱን ለመፈጸም ፈጥሮታልና፣

እስመ አእመረ ወጠየቀ ከመ እምኔሁ ይከውን ተክለ ጽድቅ ለትውልድ ዘለዓለም፣

ለዘላለም፤ የሚኖር ይስሐቅ ከሱ እንዲወለድ ስለ አወቀ ስለተረዳ፣

ወእምኔሁ ይከውን ዘርዕ ቅዱስ፣

ከሱም ክቡር ልጅ ይወለ ዳል፣

ከመ ይከውን ከማሁ ለዘገብረ ኵሉ፣

ሁሉን እንዳደረገ እንደሱ እንዲሆን።

፲፯፣ወባረካ አብርሃም ወተፈ ሥሐ፣

አብርሃምም አከበራት ደስ አለው፣

ወጸውዓ ስማ ለዛቲ በዓል በዓለ

እግዚአብሐሔር፣

ይህችን በዓል ስሟን በዓለ እግዚአብሐሔር አላት ፣

ወፍሥሓ ስጥውት ለአምላክ ልዑል፣

ልዑል እግዚአብሐሔር ደስ ብሎት የሚቀበላት በዓል አላት።

፲፰፤ወባረክናሁ ለዓለም ፤

ለዘለዓለም አከበርነው፣

ወኵሉ ዘርዐ ዘእምድኅሬሁ በኵሉ ትውልደ ምድር፤

በዚህ ዓለም ለሚኖረው ልጅ ሁሉ ከሱም በኋላ ልጁን አከበርነው፣

እስመ ገብረ ዛተ በዓለ በጊዜሃ በከመ ስምዓ ጽላተ ሰማይ ሥሩዐ ይኩን ላዕለ እሥራኤል፣

ምስክር ሆኖ እንደተጻፈ በእሥራኤል የተሠራ ይሆን ዘንድ።

፲፱፤በእንተዝ ተሠርዓ ውስተ ጽላተ ሰማይ ላዕለ እስራኤል። ስለዚህ ነገር ሥርዓት ሊሆን በመላእክት ልቡና ተጽፏል፣

ከመ ይኩኑ ገባርያነ በዓለ መጸለት ለቡዐ መዋዕለ በፍሥሐ በወርኀ ሳብዕ ፣

በሰባተኛው ወር በጥቅምት ደስ ብሏቸው ሰባት ቀን በዓለ መጸለትን የሚያከብሩ ይሆኑ ዘንድ። ይስሐቅ የተጸነሰበት ነው፣

ዘይትዌከፍ በቅድመ እግዚአብሔር ሕገ ዘለዓለም በትውልዶሙ በኵሉ ዓለማት ወዓመታት ፣

እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ባለ በዘመኑ ሁሉ ስለልጆ ቻቸው ለዘላለም ሕግ ሊሆን እግዚአብሐሔር ወዶ ሊቀበ ለው።

፳፤ወአልቦ ለዝንቱ ሕግ ወሰነ መዋዕል፣

በመዐለት ጥምቀት ገብቶበታ ልና ለዚህ ሥርዓት የተወ ሰነ ዘመን የለውም፣

እስመ ለዓለም ውእቱ ሥሩዕ ላዕለ እስራኤል ከመ ይግበርዎ፤ በዓሉን ያከብሩት ዘንድ በእ ስራኤል ላይ ለዘለዓለሙ ተጽፏልና፤

ወይገብሩ ውስተ ምጽላል፤

ድንኳን ተክለው ዳስ ጥለው ይቀመጡ ዘንድ፣

ወከመ ያንብሩ አክሊላተ ዲበ ርእሶሙ ፤

አክሊሉን በራሳቸው ይደፉ ዘንድ፤

ወከመ ይንሥኡ አጽቀ ቈጽለ ኵሑ እሙሐዝ፤

ከፈሳሹ ውሀ ዳር የአኽያ ውን እንጨት ለጋ ለጋውን ይዘው ያደርጓት ዘንድ።

፳፩፤ወነሥአ አብርሃም ልበ ጸበርት፤

በቀልተ ጸበርት ሲል ነው፤ አብርሃም ዘንባባ ያዘ፤

ወፍሬ ዕፅ ሠናይ፤

የአማረውን ዕንጨት ፍሬ ያዘ፤

ወለኵሉ ዕለት እምዕለት ሀሎ እንዘ የዓውድ ምሥዋዐ በአዕፁቅ ሰቡዐ ለለዕለት፤

ዕለት ዕለት ሰባት ቀን ዘን ባባውን ይዞ መሠዊያውን እየዞረ ከዛሬ ነገ ከነገ ማግ ሥት እያለ ያመሰግን ነበር።

፳፪፤ወበጽባሕ ይሴብሕ ወይገኒ ለአምላኩ ዘፈጠረ ኵሎ በፍ ሥሐ፤

ሁሉን ለፈጠረ ፈጣሪው ማለዳ ማለዳ ደስ ብሎት ይገዛል፤ ያመሰግናል።

፳፫፤ወበ፩ዱ ዓመት ዘሱባዔ ሐምስ ኀደገ ጥበ ይስሐቅ በዝንቱ ኢዮቤልዩ፤

በዐምስተኛው ሱባዔ በአንድ ዓመት በዚህ ኢዮቤልዩ ይስ ሐቅ ጡት መጥባት ተወ፤

፳፬፤ወገብረ አብርሃም ግዝዓ ዓቢየ በወርኀ ሣልስ በዕለተ ኀደገ ጥበ ወልዱ ይስሐቅ፤

ልጁ ይስሐቅ ጡት መጥባ ትን በተወበት ቀን በሦስተ ኛው ወር በሰኔ አብርሃም ታላቅ በዓል አደረገ፤ ወይስማኤል ወልዳ ለአጋር ግብጻ ዊት በቅድመ ገጹ ለአብርሃም አቡሁ በመካኑ፤

ከግብፅ ከመጣች አጋር የተ ወለደው ይስማኤል ባባቱ በአብርሃም ፊት በቦታው ቁሞ ነበር።

፳፭፤ወተፈሥሐ አብርሃም ወባ ረኮ ለእግዚአብሔር፤

አብርሃም ደስ አለው፤ እግዚ አብሔርንም አመሰገነው፤

እስመ ርእየ ሎቱ ፪ተ ውሉደ
ሁለት ልጆችን አይቷልና፣
ወኢሞተ ዘእንበለ ውሉድ፣

ልጅ ሳይወልድ ሳያይ አልሞ
ተምና።

፳፮፣ወተዘከረ ቃሎ ዘተናገሮ
በዕለተ ተፈልጠሎጥ እምኔሁ፣
ሎጥ ከሱ በተለየበት ቀን
የተናገረውን ቃሉን አሰበ፣
ወተፈሥሐ እስመ ወሀቦ እግዚ
አብሔር ዘርዐ በዲበ ምድር ከመ
ይረሳ ለምድር፣

ምድርን ይወርሳት ዘንድ
በዚህ ዓለም እግዚአብሔር
ልጅ ሰጥቶታልና ደስ አለው፤

ወባረኮ በአፉሁ ለፈጣሬ ኵሉ፣
ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔ
ርን በአንደበቱ አመሰገነው።

፳፯፣ወርእየቶ ሳራ ለእስማኤል
እንዘ ይትዋነይ ወይዘፍን፣

ሳራ እስማኤልን ሲጫወት
ሲዘፍን አይታ፣

ወአብርሃምኒ እንዘ ይትፌሣሕ
ዓቢየ ፍሥሓ

አብርሃምን እጅግ ደስ
ብሎት አየች፣

ወቀንአት ሶበ ርእየቶ ለይስማ
ኤል፣

እስማኤልንም ባየችው ጊዜ
ቀናች፣

ወትቤሎ ለአብርሃም ሣራ ስድዳ
ለዛቲ ወለት ወለወልዳ፣

ሳራ አብርሃምን ይህችን ልጅ
ልጇንም ስደዳት አለችው፤
እስመ ኢይወርስ ለዛቲ ወልዳ
ምስለ ወልድየ ይስሐቅ፣

የዚህች ባርያ ልጅ ከልጄ
ይስሐቅ ጋር አይወርስምና።

፳፰፣ወኀዘን ኮነ በቅድመ አዕይ
ንተ አብርሃም በእንተ ዓመቱ
ወበእንተ ወልዱ ከመ ይስድዶሙ
እምኔሁ፣

ከሱ ለይቶ ይሰዳቸው ዘንድ
ስለ ልጁ ስለ ባሪያው በአብ
ርሃም ዘንድ ኀዘን ሆነ።

፳፱፣ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብ
ርሃም ኢይኩን ኀዘን በቅድመ
አዕይንቲከ በእንተ ሕፃን ወበእንተ
ወለት፣

እግዚአብሔርም አብርሃምን
እንዲህ አለው ስለ ልጅህና
ስለ ባሪያህ በፊትህ ኃዘን
አይሁን፣

ኵሉ ዘትቤለከ ሳራ ስማዕ ንባባ ወግበር ዘትቤለከ፤

ሳራ የነገረችህን ሁሉ ሰምተህ አድርግ ፤

እስመ በይስሐቅ ይዔዋዕ ለከ ስምከ ወዘርእከ፤

ስምህ በልጅህ በይስሐቅ ይጠራልሃልና።

ወበእንተ ወልዳሰ ለዛቲ ወለት ውስተ ሕዝብ ዓቢይ ዓቢየ እሬስዮ፤

የዚችን የአጋርን ልጅ ግን ብዙ ወገን አደርገዋለሁ፤

እስመ እምዘርዕከ ውእቱ፤

እርሱ ልጅህ ነውና።

፴፤ወገይሦ አብርሃም በነግህ ነሥአ ኃባውዘ ወዝቀ ማይ ወአሰከማ ለአጋር ወለሕፃና።

አብርሃም በጧት ገሥግሦ ሄዶ፤ዳቦውን ውሀውን የያዘ ረዋቱን ልጁን አንሥቶ ለአጋር አሸከማት፤

ወፈነዋ፤

ሰደዳት፤

ወሖረት እንዘ ታንጌጊ በገዳመ ቤርሳቤ፤

በቤርሳቤ ምድረ በዳ እየተቅበዘበዘች ሄደች።

፴፩፤ወተፈጸመ ማይ እምዝቅ፤ ወህው ከረዋቱ አለቀ፤

ወፀምአ ሕፃና ወስዕነ ሐዊረ፤ ሕፃኑ ተጠምቶ መሔድ ተሳነው፤

ወወድቀ ሕፃን ወነሥአቶ እሙ፤

እስማኤል ቢወድቅ እናቱ አጋር አነሣችው፤

ወሐዊራ ገደፈቶ ታሕተ አሐቲ ኤልያስ፤

ሄዳ ከዕፀ ዘይት ስር ጣለችው ፤

ወሖረት ወነበረት አንጻሮ መጠነ አሐቲ ምንዳፈ ሐዕ፤

አንዲት ፍላፃ ወርውሮ የሚያደርስበት ያህል ርቃ በአንፃሩ ተቀመጠች፤

እስመ ትቤ ኢይርአይ ሞቶ ለሕፃንየ

የልጄን ሞት አልይ ብላለችና፤

ወነቢራ በከየት፤

ተቀምጣ አለቀሰች።

፴፪፤ወይቤላ መልአክ አሐዱ እምቅዱሳን ለምንት ትበክዪ አንቲ አጋር ፤

ከቅዱሳን መላእክት አንዱ መልአክ አንቺ አጋር ምን ያስለቅስሻል አላት፤

ወተንሢእኪ ንሥኢዮ ለሕፃን ወአኃዚዮ በእዴኪ፤

ተነሥተሽ ሕፃኑን በእጅሽ ያዥው እቀፊው፤

እስመ እግዚአብሔር ሰምዐ ቃለኪ፤

እግዚአብሔር ነገርሽን ሰምቷልና፤

ወርእዮ ለሕፃን፤

ሕፃኑንም አየው።

፴፫፤ወከሠተት አዕይንቲሃ አጋር ወርእየት ዓዘቅተ ማይ፤
አጋርም አይኗን ገልጣ የውሀውን ጉድጓድ አየች፤

ሖረት ወመልዓት ዝቃ ማየ፤

ሂዳ ረዋቱን ውሀ ሞላች፤

ወአስተየት ሕፃና፤

ልጇን አጠጣችው፤

ተንሥእት ወሖረት መንገለ በድወ ፋሪም፤

ተነሥታ ወደ ፋሪም ምድረ በዳ ሄደች።

፴፬፤ወልሕቀ ሕፃን ወኮነ ነዳፌ፤

ልጁም አደገ ፍላጻም የሚወረወር ሆነ ፤

ወሀሎ እግዚአብሔር ምስሌሁ፤

እግዚአብሔርም ከሱ ጋራ በረድኤት ነበረ፤

ወነሥአት ሎቱ እሙ ብእሲተ እምአዋልደ ግብጽ፤

እናቱ ከግብጽ ልጆች ወገን ሚስት አጋባችው ፤

ወወለደት ሎቱ ወልደ፤

ወንድ ልጅ ወለደችለት፤

ወፀውአት ስሞ ናቢዖት፤

ናቤዖትም ናቢያትም ይላል፤

እስመ ትቤ ቅሩብ ሊተ እግዚአብሔር ሶበ ፀዋዕክዎ፤

ለኔ እግዚአብሔር በጠራሁት ጊዜ ቅርብ ነው ብላለችና ስለዚህ ስሙን ናቢዖት አለችው።

## ምእራፍ ፲፱

፩፥ወኮነ በሱባዔ ሳብዕ በቀዳሚ ዓመት በወርኀ ቀዳማዊ በዝ ኢዮቤልዩ፤

በሰባተኛው ሱባኤ በመጀመሪያው ዓመት በመጀመሪያው ወር በዚህ ኢዮቤልዩ እንዲህ ሆነ፤

አመ ፲ወ፪ ለዝ ወርኀ ኮና ቃላቱ በሰማያት በእንተ አብርሃም፣ ተሰምዓ ሲል ነው፤ በዚህ ወር በዐሥራ ሁለተኛው ቀን ስለ አብርሃም ቃላት በሰማይ ተሰማ፤

ከመ ውእቱ መሐይምን በኵሉ ዘይትናገሮ፤

በሚናገረው ነገር ሁሉ የታመነ እንደሆነ፣

ወያፈቅሮ እግዚአብሔር እስመ በኵሉ ምንዳቤ ኮነ ምዕመነ፤ በመከራው ሁሉ የታመነ ሁኗልና እግዚአብሔር ይወደዋል።

፪፥ወመጽአ መኰንነ መስቴማ፣ ሁሉን የሚገዛ መስተዋድይ ሰይጣን መጣ፣

ወይቤ ቅድሜሁ ለአምላክ ናሁ አብርሃም ያፈቅሮ ለይስሐቅ ወልዱ፥፤

በጌታ ፊት እነሆ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ይወደዋል አለው፤

ወያስተኤድሞ እምኵሉ ኪያሁ፤

ከሁሉ እሱን ይወደዋል ብሎ ፤

ያዕርጎ ዲበ ምሥዋዕ ጽንሐሐ፣

በመሠዊያው ላይ መሥዋዕት ያደርገው ዘንድ ንገረው።

፫፥ወአንተ ትሬኢ ለእመ ይገብር ዘንተ ቃለ፣

ይኸነን ነገር ያደርግ እንደ ሆነ አንተ ታያለህ፤

ወተአምር ለእመ መሐይምን ውእቱ በኵሉ ዘታሜክሮ፤ በምትፈትነው ሁሉ የታመነ እንደሆነ ታውቃለህ፤ አለው፣

ወእግዚአብሔር የአምር ከመ መሐይምን ውእቱ አብርሃም በኵሉ ምንዳቤ ዘይቤሎ፤

እግዚአብሔር በነገረው፡ መከራ ሁሉ፣ አብርሃም የታመነ እንደሆነ ያውቃል፤

እስመ አመከሮ በምድሩ ወበ ዓባር፤

በምድሩ በድርቅ ፈትኖታልና፣

ወአመከሮ በብዕለ ነገሥት፤

በነገሥታቱ ገንዘብ ፈተነው፣

ወአመከሮ በብእሲቱ ካዕበ እንዘ ትትሐየድ ወበክስበት ፤ ዳግመኛም በሚስቱ መቀ ማት ፈተነው በመገረዝም ፈተነው ፤

ወአመከሮ በእስማኤል ወበአጋር አመ ፈነዎሙ፤

በሰደዳቸው ጊዜ በባሪያው በአጋርና በልጁ በእስማኤል ፈተነው፤

ወበኵሉ በዘአመከሮ ተረክበ ምእመነ።

በፈተነው መከራ ሁሉ የታ መነ ሆኖ ተገኘ፤

፲፱፤ ወኢተአንተለት ነፍሱ ፤ ሰውነቱም ቸል አላለችም፤

ኢያጕንደየ ገቢሮቶ እስመ ምዕመን ወመፍቀሬ እግዚአብሔር ውእቱ፣

እግዚአብሔርን የሚወድ የታ መነ ነውና ሥራውን አላዘገ

የም።

፳፤ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብር ሃም፣ አብርሃም አብርሃም ፤ እግዚአብሔርም አብርሃምን አብርሃም አብርሃም ብሎ ጠራው፤

ወይቤ ነየ አነ፤

አብርሃምም እነሆ ! እኔ አለሁ አለ ፤

ወይቤሎ ንሣእ ወልደከ ዘታፈቅር ይስሐቅሃ፣

የምትወደው ልጅህ ይስሐቅን ይዘህ፤

ወሑር ውስተ ደብር ልዕልት፤

ከፍ ወዳለች ተራራ ሂድ፤

ወአዕርጎ ውስተ አሐዱ እምአ ድባር ዘአነ አየድዓከ፤

ከተራሮች እኔ ወደምነግርህ ወዳንዱ ተራራ አውጣው።

፳፩፤ወአሌለየ እምሀየ አብርሃም፤ በነግህ፣

ከዚያም አብርሃም በጧት ገሠገሠ፤

ወፀዓነ ዕድግቶ፣

በቅሎውን ጭኖ፤

ወ፪ተ ደቀ ነሥአ ምስሌሁ፣

ሁለቱንም ብላቴኖቹን ከሱ ጋራ አስከትሎ፤

ወይስሐቅሃ ወልዶ፤

ልጁ ይስሐቅንም ይዞ ሄደ፤

ወዕፀወ መሥዋዕት ሠፀረ፣

ለመሥዋዕት የሚሆነውን እንጨቱን ፈልጦ አሸክሞ፤

ወሖረ ውስተ መካን በሠሉስ ዕለት፤

ሶስት ቀን እግዚአብሔር ሂድ ወዳለው ቦታ ሄደ።

፯፤ወርእየ መካነ እምርኁቅ፣

በሩቅ ሆኖ ቀራንዮን አየ፣

ወበጽሐ እስከ ዓዘቅተ ማይ፣

ከውሀ ጉድጓድ ደረሰ፤

ወይቤሎሙ ለደቂቁ ንበሩ ዝየ ምስለ ዕድግት፣

ብላቴኖቹን በቅሎውን ይዛችሁ ከዚህ ተቀመጡ አላቸው፤

ወአነ ወሕፃን ንሐውር፤

እኔና ይስሐቅ እንሄዳለን፤

ወሰጊደነ ንገብእ ኀቤክሙ፤

ሰግደን ወደ እናንተ እንመለሳለን።

፰፤ወነሥአ ዕፀወ መሥዋዕት ወአስከሞ ለይስሐቅ ወልዱ፣ መሥዋዕት የሚሠዋበትን እንጨቱን አንሥቶ ልጁን ይስሐቅን አሸከመው፤

ወነሥአ በእዴሁ እሳተ ወመጥባሕተ፣

በእጁ እሳቱን በጉን የሚያርድበት ቢላዋውን ይዞ፣

ወሖሩ ኅቡረ ፪ ኤሆሙ እስከ ውእቱ መካን፣

ሁለቱም አንድ ሁነው እስከ ቀራንዮ ድረስ ሄዱ።

፱፤ወይቤሎ ይስሐቅ ለአቡሁ አባ፤

ይስሐቅም አባቱ አብርሃምን አባቴ ! አለው፣

ወይቤሎ አቡሁ ነየ አነ ወልድየ፣

ልጄ እነሆኝ አለሁ አለው፣

ናሁ እሳት ወመጥባሕት ወዕፀው፣

እሬኢ ያለበት ነው፤ እነሆ እሳቱን ዕንጨቱን በጉ የሚታረድበት ወቀለምቱን አያለሁ፤

ወአይቴ በግዕ ዘለጽንሐሕ፣

አባቴ ! ለመሥዋዕት የሚሆ ነው በግ ወዴት ነው አለው።

፯፤ ወይቤሎ አቡሁ እግዚአብሔር ይሬኢ ሎቱ በግዐ ለጽንሐሕ ወልድየ፤

ልጄ ለመሥዋዕት የሚሆን ውንስ በግ እግዚአብሔር ያውቃል አለው፤

ወቀርበ ኀበ መካን ዘደብረ እግዚአብሔር፣

አብርሃም እግዚአብሔር ወደ ታየበት ተራራ ቀረበ፣

ወሐነፀ ምሥዋዐ፣

መሠዊያውን ሠራ።

ወአንበረ ዕፀወ ዲበ ምሥዋዕ ፤

እንጨቱን በመሠዊያው ላይ ከመረው፤

ወአሠረ ይስሐቅሃ ወልዶ፣

ልጁን ይስሐቅን አሠሮ፣

ወአንበሮ ዲበ ዕፀው ዘመልዕልተ ምሥዋዕ ፤

በመሠዊያው ላይ ካለው እን ጨት ላይ አስተኛው።

፲፩፤ ወሰፍሐ እዴሁ ይንሣእ መጥባሕተ ከመ ይዝብሖ ለይስ ሐቅ ወልዱ፣

ልጁ ይስሐቅን ይሠዋው ዘንድ ሾተሉን ለማንሣት እጁን ዘረጋ ፤

ወአነ ቆምኩ ቅድሜሁ ወቅ ድመ መኰንን መስቴማ ፤ በአብርሃምና በሰይጣን መካ ከል ቆምኩ።

፲፪፤ ወይቤ እግዚአብሔር በሎ ኢያውርድ እዴሁ ላዕለ ሕፃን፣ ይስሐቅን እንዳይሠዋው ንገ ረው አለ፤

ወኢይግበር ላዕሌሁ ምንተኒ ፡

በሱ ላይ ምን ምን ክፉ ነገር እንዳያደርግ ንገረው አለ ፣

እስመ አእመርኩ ከመ ፈራኄ እግ ዚአብሔር ውእቱ፣

እግዚአብሔርን የሚፈራ የሚ ያመልክ እንደሆነ አውቄአለ ሁና።

፲፫፤ ወፀዋዕክዎ እምሰማይ ወእ ቤሎ አብርሃም አብርሃም፣

ከሰማይ ሁኜ አብርሃም አብ ርሃም ብዬ ጠራሁት፤

ወደንገጸ አብርሃም ወይቤ ነየ አነ፤

አብርሃም ደንግጦ እነሆ እኔ አለሁ አለ፤

ወእቤሎ ኢትፌኑ እዴከ ላዕለ ሕፃን፤

እጅህን በይስሐቅ ላይ አትዘ ርጋ፤

ወኢትግበር ምንተኒ ዲቤሁ፤

በሱ ላይ ምንም ምን ክፉ ነገር አታድርግ፤

እስመ ይእዜ አእመርኩ ከመ ፈራሄ እግዚአብሔር አንተ፤

አንተ እግዚአብሔርን የምት ፈራ እንደሆንክ ዛሬ አውቄ አለሁና፤

ወኢመሐከ ወልደከ ወበኵረከ እምኔየ፤

ከኔ ይልቅ ለበኽር ልጅህ ለይስሐቅ አላዘንህለትምና፤ ወተሐፍረ መኩንን መስቴማ፤

ሁሉን በተንኮል የሚገዛ ሰይጣን አፈረ።

፲፬፤ ወአንሥአ አብርሃም አዕይን ቲሁ ወርእየ፤

አብርሃም አንገቱን አቅንቶ አየ፤

ወናሁ አሐዱ በሐኰ እኁዝ በዕፀ ሳቤቅ ወይመጽእ በአቅርንቲሁ፤ እነሆ አንድ የበግ አውራ ቀንድና ቀንዱን በዕፀሳቤቅ ተይዞ ሲመጣ አየ፤

ወሖረ አብርሃም ወነሥኦ ለበ ሐኰ፤

አብርሃም ሄዶ በጉን አመጣ፤

ወአዕረጎ ለጽንሐሕ ህየንተ ወልዱ፤

ስለ ልጁ ፈንታ መሥዋዕት ሊሆን ሠዋው።

፲፭፤ ወጸውአ አብርሃም ለውእቱ መካን ራእየ እግዚአብሔር፤ አብርሃም ያንን ቦታ እግዚአ ብሔር የታየበት አለው፤

ከመ ይትበሀል እግዚአብሔርሃ ርእኩ፤

እግዚአብሔርን ያየሁበት ቦታ ይባል ዘንድ፤

ወውእቱ ደብረ ጽዮን፤

ይህም የጽዮን ተራራ የተባ ለው ቀራንዮ ነው።

፲፮፤ወጸውኦ እግዚአብሔር ለአብ
ርሃም በስሙ ዳግመ እምሰማይ፤
እግዚአብሔር ከሰማይ ሆኖ
ሁለተኛ አብርሃምን በስሙ
ጠራው፤

በከመ አስተርአይናሁ ከመ ንትና
ገሮ በስመ እግዚአብሔር፤

እኛ እንደታየነው በእግዚአብ
ሔር ስም እንናገረው ዘንድ፤
ወይቤ በርእስየ አማንየ መሐልኩ
ይቤ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር በእውነት እኔ
በራሴ ማልኩ አለ አልነው።

፲፯፤እስመ ገበርከ ዘንተ ቃለ፤

ይህን ነገር አድርገሀልና፤

ወኢመሐከ ወልደከ በኵረከ እም
ኔየ ዘአፍቀርከ፤

ከኔ ይልቅ ለወደድከው ለበ
ኵር ልጅህ አላዘንህምና፤

ከመ ባርኮ እባርከ ለከ ወአብዝኖ
እስተባዝኖ ዘርዓከ፤

ፈጽሜ አከብርሃለሁ፤ ፈጽሜ
ልጅህን አበዛልህአለሁ፤

ከመ ከዋክብተ ሰማይ ወከመ ኖፃ
ዘድንጋገ ባሕር፤

በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ
እንደ ሰማይ ኮከብ ልጅህን
አበዛልሀለሁ።

፲፰፤ወይወርሱ ዘርዕከ አህጉረ
ፀሮሙ፤

ልጆችህ የጠላቶቻቸውን ሀገር
ይወርሳሉ፤

ወይትባረኩ በዘርዕከ ኵሎሙ
አሕዛበ ምድር ህየንተ ዘሰማዕከ
ቃለ ዚአየ፤

የኔን ነገር ስለ ሰማህ በዚህ
ዓለም ያሉ አሕዛብ በአንተ
ይከብራሉ፤

ወአይዳዕኩ ለኵሉ ከመ ምእመን
አንተ ሊተ በኵሉ ዘእቤለከ፤

እኔ በነገርኩህ ነገር ሁሉ
አንተ የታመንህ እንደሆንክ
ለሰው ሁሉ ተናገርኩ፤

ሖረ በሰላም፤

በፍቅር፤ በደስታ ሄድ አለው።

፲፱፤ወሖረ በሰላም አብርሃም ኀበ
ደቂ፤

አብርሃምም በፍቅር፤ በደ
ስታ ወደ ብላቴኖቹ ሄደ፤

ተንሥኡ ወሖሩ ቤርሳቤ ኅቡረ፣

ተነሥተው በአንድነት ወደ ቤርሳቤ ሄዱ፤

ወኃደረ አብርሃም ኅበ ዓዘቅተ መሐላ፣

አብርሃም በዓዘቅተ መሐላ በውሀ ጉድጓድ ዘንድ አደረ፣

ወገብረ ዛተ በዓለ በኵሉ ዓመታት ሰቡዐ ዕለተ በፍሥሐ፣

ይህችን በዓል በዘመኑ ሁሉ ሰባት ቀን በደስታ በዓል አደረጋት።

ወሰመያ በዓለ እግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔር በዓል አላት፤

በከመ ሰቡዕ ዕለት እለ ሖረ፤

እንደ ሔደባቸው እንደ ሰባቱ ዕለታት፤

ወተመይጠ በሰላም፣

በፍቅር፣ በደስታ እንደተመለሰባቸው።

፳፮፤ወከመዝ ውእቱ ሥሩዕ ወጽሑፍ ውስተ ጽላተ ሰማይ፤ በመላእክት ልቡና እንዲህ ተጽፏል ታገዟል፤

በእንተ እስራኤል ወዲበ ዘርዑ፤

በእስራኤል በልጆቹም ታዘ አል፤

ለገቢረ ዛቲ በዓል ሰቡዓ ዕለተ በፍሥሐ ወገብረ በዓለ በትፍሥሕት፣

ይህችን በዓል ሰባት ቀን በደስታ በዓል ለማድረግ ተጽፏል።

፳፩፤ወበዓመት አሐዱ ዘሱባዔ ቀዳማዊ በዘ፵ወ፪ ኢዮቤልዩ፣
በመጀመሪያው ሱባዔ በአንድ ዓመት በዐርባ ሁለተኛው ኢዮቤልዩ፣

ተመይጠ አብርሃም ወኀደረ አንጻረ ኬብሮን፣

አብርሃም ተመልሶ በኬብሮን አንጻር አደረ፣

ዛቲ ይእቲ ቃርያታርባቅ፤

ይህችም ቃርያታርባቅ የምትባል ቦታ ናት፤

፪ተ ሱባኤ ዓመት፤

ሁለት የሱባዔ ዘመን ኖረ ተቀመጠ።

፳፪፡ወበዓመት ቀዳሚ ዘሱባዔ ሣልስ ዘዝ ኢዮቤልዩ፤

በዚህ ኢዮቤልዩ በሶስተኛው ሱባዔ በመጀመሪያው ዓመት፤

ተፈጸመ መዋዕለ ሕይወታ ለሳራ፤

ሳራ በሕይወት የምትኖርበት ዘመን ተፈጸመ፤

ወሞተት በኬብሮን፤

በኬብሮን ሞተች።

፳፫፡ወሖረ አብርሃም ከመ ይብክያ ወይቅብራ፤

አብርሃም አልቅሶ ይቀብራት ዘንድ ሄደ፤

ወናሜክሮ እመ ይትዔገሥ መንፈሱ፤

ልቡናው ይታገሥ እንደሆነ እንፈትነዋለን፤

ወኢይትአንተል በቃለ አፉሁ፤ ከቃሉ በወጣ ነገር ችላ የማይል እንደሆነ እንፈትነዋለን፤

ወተረክበ በዝኒ ዕጉሠ፤

በዚህም የታገሠ ሆኖ ተገኘ፤

ወኢተሀውከ፤

አልተበሳጨም፤

እስመ በትዕግሥተ መንፈሱ ተናገረ፤ ምስለ ደቂቀ ኬጢ፤

በልቡናው ትዕግሥት ከኬጢ ልጆች ጋራ ተነጋግሮአልና፤

ከመ የሀብዎ መካነ፤

ቦታ ይሰጡት ዘንድ ፤

ከመ ይቅብር በድና ውስቴቱ ፤

በውስጡ ሬሳውን ይቀብር ዘንድ።

፳፬፡ወእግዚአብሔር ሞገሰ ወሀበ ሎቱ በቅድመ ኵሉሙ እለ ይሬእይዎ፤

እግዚአብሔርም በሚያዩት ሰዎች ሁሉ ፊት ባለሟልነትን ሰጠው፤

ወአስተብቍዐ አብርሃም በየውሀት እምኀበ ደቂቀ ኬጢ፤

ከኬጢ ልጆች በየዋህነት በውነት ለመነ፤

ወወሀብዎ ምድረ በዓት ዘካዕበት፤

እጥፍነት ያላት ዋሻ ያለባትን ምድር ሰጡት፤

ዘእንጻረ ማምብራም ፤

ወይራ፣ ግራር ባለበት አን ጻር፤እንድም አብርሃም ይቀ መጥባት በነበረ አንጻር ያለች።

እንተይእቲ ኬብሮን፤

ይህችም ኬብሮን ናት፤

በማብሩር፣

በዓርባ ብር ሸጡለት፤ ምነው ዐራት መቶ አይደለም፥ ቢሉ መቶውን ዐሥር መቶውን ዐሥር ብሎ እንዲህ አለ።

፳፭፤ወእሙንቱሂ ያስተበቍዕዎ እንዘ ይብሉ ንሁበከ በከ፤

እነሱም ያለ ዋጋ እንስጥህ ብለው ለመኑት፤

ወውእቱሰ ኢነሥአ እምእዴሆሙ በከ፤

እሱ ግን ያለ ዋጋ ከነዚያ እጅ አልወሰደም፤

እስመ ወሀበ ሤጦ ለመካን ብሩረ ፍጹመ ፤

የቦታውን ዋጋ ብሩን ፈጽሞ ሰጠ እንጂ፤

ወሰገደ ሎሙ ካዕበ፤

ዳግመኛ ሰገደላቸው።

፳፮፤ወእምዝ ቀበረ በድኖ ውስተ በአዓት ዘካዕበት፣

ከዚህ በኋላ እጥፍነት ባላት ዋሻ ሬሳውን ቀበረ፤

ወኮነ ኵሉ መዋዕለ ሕይወታ ለሳራ ፻ወ፳ ወ፯ተ፣

የሳራ መላ ዘመንዋ መቶ ሃያ ሰባት ሆነ፤

ወእሉ ፪ቱ ኢዮቤልዩ ወ፬ቱ ሱባዔ ወ፩ዓመት፤

እኒህም ሁለት ኢዮቤልዩ አራት ሱባዔ አንድ ዓመት ናቸው፤

ዝንቱ መዋዕለ ዓመታተ ሕይወታ ለሳራ፤

ሳራ በሕይወት የኖረችበት የዘመኗ ወራት ይህ ነው፣ መቶው ዘመን ሁለት ኢዮቤልዩ ሆኖ ሁለቱን ዓመት ከሀያ ሰባቱ ቢገፕ ሙት ሃያ ዘጠኝ ይሆናል ይህንም በሱባዔ ቢገቡት አራት ሱባዔ ሆኖ አንድ ዓመት ይተርፋል

፳፯፤ወዝ መከራ ዐሥር በዘተመ ከረ ቦቱ አብርሃም፣

አብርሃም በተፈተነበት ገን ዘብ ያገኘው ዐሥሩ መከራ ይህ ነው፤

፳፯፤ወዝ መከራ ዐሥር በዘተመ ከረ ቦቱ አብርሃም፣

አብርሃም በተፈተነበት ገን ዘብ ያገኘው ዐሥሩ መከራ ይህ ነው፤

ወተረክበ ቦቱ ምዕመነ ወዕጉሠ መንፈስ ፤

ልበ ሰፊ የታመነ ሆኖ የተ ገኘበት ይህ ነው፤

ወኢይቤ ቃለ በእንተ ንባብ ዘበምድር ዘይቤ እግዚአብሔር የሀቦ ኪያሃ ሎቱ ወለዘርዑ እምድኅሬሁ፣

ለሱ ፤ ከሱም በኋላ ለልጆቹ እሷን ይሰጠው ዘንድ እግዚ አብሔር የነገረውን ነገር አይሆንም አላለም፣

ወመካነ አስተብቍዐ በህየ ከመ ይቅብር በድኖ ፤

ሬሳውን ይቀብር ዘንድ መቃ ብር ለመነ፤

እስመ ተረክበ መሐይምነ ወዕ ጉሠ፣

የታመነ ዕጉሥ ሆኖ ተገኝ ቷልና፤

ወተጽሕፈ አርከ እግዚአብሔር ውስተ ጽላተ ሰማይ፤

በመላእክት ልቡና የእግዚአ ብሔር ወዳጅ ተብሎ ተጻፈ።

፳፰፤ወበዓመት ራብዕ ሎቱ ነሥአ ለይስሐቅ ወልዱ ብእሲተ፣ ባራተኛው ዘመን ለልጁ ለይስሐቅ ሚስትን አመጣ ለት፤

ወስማ ርብቃ፤

ስሟም ርብቃ ይባላል፤

ወለተ ባቱኤል ወልደ ናኮር እኁወ አብርሃም እኅተ ላባ፣

ይቺውም የላባ እኅት የአብ ርሃም ወንድም የናኮር ሚስት የሚልካ ልጅ ናት፣

ወባቱኤል ወልደ ሚልካ ብእሲተ ናኮር እኁወ አብርሃም ወለዶሙ፣ ለላባ ወለርብቃ፤

የአብርሃም ወንድም የሆነ የናኮር ሚስት የሚልካ ልጅ ባቱኤልም ርብቃንና ላባን ወለዳቸው።

፳፱፤ ወአብርሃም ነሥአ ሎቱ ብእሲተ ሣልሲተ ፤

አብርሃምም ሶስተኛ ሚስትን አገባ ፤

ወስማ ኬጡራ ፤

ስሟም ኬጡራ የምትባል ናት፤

እምነ ውሉደ ልደ ቤቱ ፤

ከቤቱ ከተወለዱ ልጆች ወገን የምትሆን ፤

እመ ሞተት አጋር እምቅድመ ሳራ፤

ከሳራ አስቀድማ አጋር በሞተች ጊዜ ፤

ወይእቲኒ ወለደት ሎቱ ውሉደ ስድስተ ፤

ይቺውም ስድስት ወንዶች ልጆችን ወለደችለት ፤

ዘንበሪሃ ወዮክሳንሃ ወማዳይሃ ወማዳንሃ ወኢያዝቦቅሃ ወስሂያሃ፤

ዘንበሪን፣ ዮክሳንን፣ ማዳይን፣ ማዳንን፣ ኢያዝቦቅን ስሂያንን፤ እነዚህን ሁሉ ወለደችለት።

፴፤ በ፪ቱ ሱባዔ ዓመት ወበሱባዔ ሳድስ ወበ፪ቱ ዓመት ፤

በሁለት ሱባዔ ዘመን በስድስተኛው ሱባዔ ፤ በሁለተኛው ዓመት ፤

ወለደት ርብቃ ለይስሐቅ ፪ደቂቀ ያዕቆብሃ ወኤሳውሃ ፤

ርብቃ ለይስሐቅ ያዕቆብን ኤሳውን ሁለቱን ልጆች ወለደችለት።

፴፩፤ ወያዕቆብሰ ፍጹም ወራትዕ፤

ያዕቆብ ግን ፍጹም ቅን ነበር፤

ወኤሳውሰ ውእቱ ብእሲ ድሩክ ወነቃላዊ ወጸጓር ፤

ኤሳው ግን ጽኑእ ሰው ቀማኛ ጠጉራም ሰው ነበር፤

ወያዕቆብ የኀድር ውስተ ምጽላላት፤

ያዕቆብ ቤት ለቤት ይውላል፤

ወልሕቁ ወራዙት ፤

እነዚህ ሕፃናትም አደጉ ።

፴፪፤ ወተምህረ ያዕቆብ መጽሐፈ፤

ያዕቆብ መጽሐፈ አበውን ተማረ፤

ወኤሳውሰ ኢተምሕረ ፤

ኤሳው ግን አልተማረም ፤ እስመ ብእሲ ሐቃላዊ ውእቱ ወነአዊ ፤

አርበኛ፤ አዳኝ ሰው ነበርና ፤

ወተምህረ ጸብአ ፤

ሰልፍን ተማረ ፤

ወኵሎ ግብረ ድሩክ ፤

የጸናውን ሥራ ሁሉ ተማረ፤

ወያፈቅር ያዕቆብሃ አብርሃም ፤

አብርሃም ያዕቆብን ይወድ ነበር፤

ወይስሐቅ ኤሳውሃ ፤

ይስሐቅ ኤሳውን ይወድ ነበር።

፴፫፤ ወርእየ አብርሃም ግብሮ ለኤሳው ፤

አብርሃም የኤሳውን ሥራ አየ፤

ወአእመረ ከመ በያዕቆብ ይፄዋዕ ሎቱ ስም ወዘርዕ ፤

ነገር ግን ስም ልጅ በያዕቆብ እንዲጠራለት አወቀ ።

፴፬ ወጸውዓ ለርብቃ ወአዘዛ በእንተ ያዕቆብ ፤

ርብቃን ጠርቶ የያዕቆብን ነገር አዘዛት ፤

እስመ ርእየ ከመ ይእቲ ታፈቅሮ ለያዕቆብ ፈጽፋደ እምነ ኤሳው ፤

ከኤሳው ይልቅ ፈጽማ እሷ ያዕቆብን እንድትወደው አይ ቷልና።

፴፭፤ ወይቤላ ወለትየ ዕቀቢ ወልድየ ያዕቆብሃ ፤

ልጄ ! ያዕቆብን ተንከባክበሽ አሳድጊልኝ አላት ፤

እስመ ውእቱ ይከውን ህየንቴየ ዲበ ምድር ለበረከት በማዕከለ ውሉደ ሰብእ ፤

እሱ በዚህ ዓለም ስለ እኔ ፈንታ በሰዎች ልጆች መካከል ለበረከት ይሆናልና፤

ወለኵሉ ዘርዓ ሴም በትምክህት፤

ለሴም ልጆች መመኪያ ይሆ ናል ፤

እስመ አአምር ከመ ኪያሁ የኀሪ እግዚአብሔር ሎቱ ለሕዝብ ቃውም እምኵሎሙ እለ ዲበ ገጸ ለምድር፤

በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ሰዎች ይልቅ ለሕዝቡ ጠበቃ ሊሆን እግዚአብሔር እሱን እንዲመ ርጥ አውቃለሁና ልጄ ያዕቆ ብን ጠብቂ አላት ።

፴፮፤ ወናሁ ይስሐቅ ወልድየ ያፈቅሮ ለኤሳው እምያዕቆብ ፤

እነሆ ልጄ ይስሐቅ ከልጁ ከያዕ

ቆብ ይልቅ ኤሳውን ይወዳል፣

ወአነ እሬእየኪ መፍቀሪተ ጻድቅ ያዕቆብ ፤

እኔም ደግ ሰው ያዕቆብን ስት ወድው አይሻለሁ ፣

ወስኪ ዓዲ አሠንዮ ላዕሌሁ ፣

ዳግመኛም በጎ ማድረግን በሱ ላይ ጨምሪለት።

፴፯፤ ወይኩና አዕይንትኪ ላዕሌሁ ለፍቁር ፣

ዓይነ ልቡናሽ በያዕቆብ ላይ ጸንቶ ይኑር ፣

እስመ ውእቱ ይከውነኪ ለበረከት ዲበ ምድር እምይእዜ ወእስከ ለዓለም ፣

ከዛሬ ጀምሮ ለዘለዓለሙ እሱ ለበረከት ይሆነኛልና ፣

ወእስከ ኵሉ ትውልደ ዓለም ፣ እስከ ልጅ ልጅ ዘመንም ድረስ ፣

ወይጽናዕ እደውኪ፣

ቃልሽ ለመምከር ይጽና ፣

ወትትፌሣሕ ልብኪ በወልድኪ ያዕቆብ ፣

ልቡናሽ በልጅሽ ያዕቆብ ደስ ይላታል ፣

እስመ ኪያሁ አፍቀርኩ ፈድፋደ እምኵሎሙ ውሉድየ ፣

ከልጆቼ ሁሉ ፈጽሜ እሱን ወድጄአለሁና ፣

እስመ ለዓለም ይትባረክ ወዘርዑ ይከውን ዘይመልእ ኵላ ምድረ ፣

ለዘላለም ይከብራል ልጁም ይህችን ዓለም የሚመላት ይሆናልና ፣

እመ ይክል ሰብእ ኆልቆ ኆፃ ባሕር ከማሁ ይትኌለቁ ዘርዑሂ ፣

ሰው የባሕር አሸዋን መቍጠር ቢችል ልጆቹ እንደዚህ ይቆጠራሉ ፣ አንድም የባሕር አሸዋ እንዳይቆጠር ልጆቹ እንደዚሁ አይቆጠሩም።

፴፰፤ ወኵሎን በረከታተ እለ ባረከኒ እግዚአብሔር ኪያየ ወዘርዕየ፣

እግዚአብሔር እኔን ልጄን ያከበረባቸው በረከታት ፣

ለያዕቆብ ወለዘርዑ ይኩን ኵሎ መዋዕለ ፣

ባለ በዘመኑ ሁሉ ለያዕቆብና ለልጁ ይሁኑ፣

ወበዘርዑ ይትባረክ ስምየ ወስመ አበውየ ሴም ወኖኅ ወሄኖክ ወመ ላልኤል ወሄኖስ ወሴት ወአዳም ፤

በሱ ልጅ የኔ ስም የአባቶቼ የሴም የኖኅ የሄኖክ የመላል ኤል የሄኖስ የሴት የአዳም ስም ይከብራል፣

ወእሙንቱ ይከውኑ ለሣርሮ ሰማይ ወለአጽንኦ ምድር ፤

እነዚህም ሰማይን ምድርንም ለማጽናት ይሆናሉ በወትሮ ግብራቸው እንዲህ አለ ፤

ወለሐድሶ ኵሉ ብርሃናት ዘዲበ ምጽንአት ፤

በሰማይ ላይ ያሉ ብርሃናትን ለማጽናት፣እመልዕልተ ምጽን ዓት ቢል ከጠፈር በላይ የሚ ገኘውን በረከት ሰጥቶ ያክብ ርህ።

፴፱፤ ወጸውአ ለያዕቆብ በቅድመ አዕይንቲሃ ለርብቃ እሙ ፤

ያዕቆብን በናቱ ርብቃ ፊት ጠራው፤

ወሰዓሞ ወባረኮ ፤

ሳመው መረቀው ፤

ወይቤ ወልድየ ያዕቆብ ፍቁር ዘአ ፍቀረተከ ነፍስየ ፤

ልቡናየ የወደደችህ ልጄ ወዳጄ ያዕቆብ ፤

ይባርከ እግዚአብሔር እመልዕልተ ምጽና ዓት ፤

ከጠፈር በላይ ያለ ፈጣሪ ያክ ብርህ።

፵፤ ወየሀብከ ኵሉን በረከታተ እለ ባረከ አዳምሃ ወሄኖክሃ ወኖኅሃ ወሴምሃ ፤

ሴምን ኖኅን ሄኖክን አዳምን ያከበረባቸው በረከቶችን ይስ ጥህ፣

ወኵሎ ዘመጠነ ተናገረኒ ወኵሎ ዘመጠነ የሀበኒ ፤

ለኔ የነገረኝን ሁሉ ለኔ እሰጥ ሀለሁ ያለኝን ሁሉ ፤

ያጥግዕ ላዕሌከ ወላዕለ ዘርዕከ እስከ ለዓለም ፤

ያኅድር ያጽንእ ሲል ነው ፤

በአንተ ላይ በልጆችህም ላይ ለዘላለም ያሳድረው ፤

በከመ መዋዕለ ሰማይ ዲበ ምድር፤

ሰማይ በአድማስ ላይ ጸንቶ የኖረውን ያህል።

፴፮፤ ወኢይመብሉ ላዕሌከ ወላ
ዕለ ዘርዕከ መናፍስተ መስቴማ ፤

የዲያብሎስ ሠራዊት በአን
ተም በልጆችህም ላይ አይሰለ
ጥኑም አይሰልጥኑ ፤

ከመ ያርኀቁከ እምድኅረ እግዚ
አብሔር ፤

እግዚአብሔርን ከአምልኮ ከመ
ከተል ያርቁህ ዘንድ ፤

ዘውእቱ አምላክከ እምይእዜ ወእ
ስከ ለዓለም ፤

ይኸውም ከዛሬ ጀምሮ ለዘለ
ዓለም የምታመልከው ፈጣሪህ
ነው።

፴፯፤ ወይኩንከ እግዚአብሔር
አምላከ ወአበ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር አባት
ይሁንህ ፤

ወአንተሂ ወልደ ፤

አንተም ልጅን ሁነው ፤

ወበኵረ ለሕዝብ ኵሉ መዋዕለ ፤

ባለ ዘመንህ ሁሉ አንተም
ለሕዝቡ አለቃ ሁን ፤

ወሑር ወልድየ በሰላም ፤

ልጄ በፍቅር በደስታ ኑር።

፴፰፤ ወወጽኡ ፪ኤሆሙ ኅቡረ
እምኅበ አብርሃም ፤

ሁለቱም ርብቃና ያዕቆብ አንድ
ሁነው ከአብርሃም ዘንድ ወጡ፤

ወአፍቀረቶ ርብቃ ለያዕቆብ በኵሉ
ልባ ወበኵሉ መንፈሳ ፤

በፍጹም ልቧ በፍጹም ሰው
ነቷ ርብቃ ያዕቆብን ወደደ
ችው ፤

ወብዙኀ ፈድፋደ እምነ ኤሳው ፤

ከኤሳው ይልቅ ፈጽማ ወደደ
ችው ፤

ወይስሐቅ ያፈቅሮ ለኤሳው ፈድ
ፋደ እምያዕቆብ ፤

ይስሐቅ ከያዕቆበ ይልቅ ኤሳ
ውን ይወድ ነበር።

## ጉባኤ

፴፱፤ ወበ ፵ወ፪ ኢዮቤልዩ በዓ
መት ቀዳሚ ዘሱባዔ ሳብዕ ፤

በዓርባ ሁለተኛው ኢዮቤልዩ
በሰባተኛው ሱባዔ በመጀመ
ሪያው ዓመት ፤

ጸውዐ አብርሃም እስማኤልሃ ወ፲ተ
ወ፪ተ ደቆ ፤

አብርሃም እስማኤልንና ዐሥራ
ሁለቱን ልጆቹን ፤

ወይስሐቅሃ ፧

ይስሐቅን ፧

ወ፪ኤሆሙ ደቂቆ ፧

ሁለቱን ልጆቹን ፧

ወ፮ቱ ደቂቀ ኬጡራ ፧

የኬጡራን ልጆች ስድስቱን ፧

ወውሉዶሙ ፧

ልጆቻቸውን ሁሉ ጠራ።

፪፡ ወአዘዞሙ ከመ ይዕቀቡ ፍኖተ እግዚአብሔር ፧

ሕገ እግዚአብሔርን ይጠብቁ ዘንድ አዘዛቸው ፧

ወከመ ይግበሩ ጽድቀ ፧

በጎ ሥራን ይሠሩ ዘንድ አዘዛቸው ፧

ወያፍቅር ፩ዱ ፩ዱ ቢጾ ፧

አንዱም አንዱ ባልንጀራውን ይወድ ዘንድ ፧

ከመ ይኩኑ ከማሁ በውስተ ኵሉ ፀብእ ከመ ይሑሩ ፩፩ዱ ላዕሌሆሙ ዲበ አሐዱ አሐዱ ፧

እንደዚህም ሁሉ በሰልፍ ጊዜ በአንዱ ላይ አንዱ ጸንቶ ይኖር ዘንድ አዘዛቸው።

፫፡ ወለገቢረ ፍትሕ ወጽድቅ በዲበ ምድር ፧

በዚህ ዓለም እውነት ፍርድን ለመፍረድ ፧

እውነት ነገርን ለመናገር ፧

ወከመ ይክስቡ ውሉዶሙ በኪዳን እንተ ተካየድነ ምስሌሆሙ ፧

ከነሳቸው ጋራ በተማማልነው መሐላ ልጆቻቸውን ይገርዙ ዘንድ ፧

ወከመ ኢይትዓደዉ የማነ ወፀጋመ እምኵሉን ፍናዊሁ ዘአዘዘነ እግዚ አብሔር ፧

እግዚአብሔር ካዘዘን ሥራ ሁሉ ወደቀኝም ሁኖ ወደግ ራም ሆኖ እንዳይተላለፉ ፧

የማንን ጠልቶ አይደለም ፀጋ ምን ሲአይ ነው እንጂ ፧

ከመ ንትዐቀብ እምኵሉ ዝሙት ወርኵስ ፧

ከዝሙት ከጣዖት እንጠበቅ ዘንድ ፧

ወከመ ንኅድግ እማእከሌነ ኵሎ ርኵሰ ወዝሙተ ፧

ዝሙትንና ጣዖትን ከመካከላ ችን እናርቅ ዘንድ ካዘዘን ሕግ ሁሉ እንዳይወጡ አዘዛቸው።

፵፯፤ ወአመ ዘመወት ለከሙ ኵላ ብእሲት ወእመኒ ወለት አው ዕይዋ በእሳት ፤

ሴት ሁሉ ብትሰስንባችሁ ልጅም ብትሆን በእሳት አቃ ጥሏት ፤

ወኢይዘምዋ ድኅረ አዕይንቲሆን ወልቦንሂ ፤

ልባቸው ባሰበው ዓይናቸው ባየው እንዳይስቱ ፤

ወበዕደዊሆሙ ከመ ኢይንሥኡ ሎሙ ብእሲተ እምአዋልደ ከነአን ፤

ወንዶች ከከነአን ልጆች ሚስት ይሆኗቸው ዘንድ እን ዳይወስዱ ፤

እስመ ይሤረዉ ዘርዓ ከነአን እምድር ፤

የከነአን ልጆች ከዚህ ዓለም ይጠፋሉና።

፵፰ ወነገሮሙ ኵነኔሆሙ ለረ ዓይት ፤

በደቂቀ ሴት የተፈረደባቸውን ፍርድ ነገራቸው ፤

ወኵነኔ ሰዶም፤

በሰዶም የተፈረደውንም ነገራ ቸው ፤

ከመ ተኩነኑ በእንተ እከዮሙ ፤

በኀጢአታቸው ምክንያት እን ደተፈረደባቸው ፤

ወበእንተ ዝሙት ወርኵስ ፤

ኃጢአት ስለ ሠሩ ፤ ጣዖት ስለ አመለኩ ፤

ወሙስና በበይናቲሆሙ ወበዝሙት ሞቱ ፤

እርስ በእርሳቸው በሚሠሩት በዝሙት ምክንያት ጥፋት እንዳገኛቸው ነገራቸው።

፵፱፤ ወአንትሙኒ ተዐቀቡ እም ኵሉ ዝሙት ወርኵስ ፤

እናንተም ዝሙትን ከመሥ ራት ጣዖትን ከማምለክ ተጠ በቁ ፤

ወእምኵሉ ግማኔ ኀጢአት ፤

ኃጢአትን አብዝቶ ከመሥ ራት፤

ከመ ኢተሀቡ ስመነ ለመርገም ፤

ስማችንን እንዳታስነቅፉ ፤ ወኵሎ ሕይወተክሙ ለትምክህት ፤

አኗኗራችሁን ሁሉ ለትምክ ህት እንዳታደርጉ ፤

ወኵሎ ውሉደክሙ ለሙስና በሰይፍ ፤

ልጆቻችሁንም በሰይፍ እንዲጠፉ አታድርጉ ፤

ወትከውኑ ርጉማነ ከመ ሰዶም ፤

እንደ ሰዶም የተረገማችሁ ትሆናላችሁ፤

ወኵሉ ተረፍክሙ ከመ ውሉደ ገሞራ ፤

ልጆቻችሁ ሁሉ እንደ ገሞራ ልጆች ይሆናሉ።

፶፤ ወአነ አሰምዕ ለክሙ ውሉድየ፤

ልጆቼ! እኔ አዳኝባችኋለሁ፤

ወአፍቅርዎ ለአምላከ ሰማይ ፤

ሰማይን የፈጠረ እግዚአብሔርን ውደዱት ፤

ወተፀመዱ ኵሎ ትእዛዞ ፤

ትእዛዙን ሁሉ እንደ በሬ ጽምድ ሁናችሁ ጠብቁ ፤

ወኢትሑሩ ድኅረ ጣዖቶሙ ወድኅረ ርኵሶሙ ፤

እነዚያ የሚሠሩትን ኃጢአት አትሥሩ ፤ የሚአመልኩትንም ጣዖት አታ ምልኩ ፤

ወአማልክተ ስብኮ ኢትግበሩ ለክሙ፤

ተመትቶ የተሠራ ጣዖትን አታምልኩ ፤

ወግልፎዋተ ፤

የተቀረፀ ጣዖትን አትሥሩ ፤

እስመ ከንቱ ውእቱ ወኢምንትኒ መንፈስ አልቦሙ ፤

ከንቱ ነውና ምንም እስትንፋስ የላቸውምና ፤

እስመ ግብረ ዕደው እሙንቱ ፤

የእጅ ሥራ ናቸውና ፤

ወኵሎሙ እለ ይትዌከሉ በሙ ፤

የሚያምኑባቸው ሰዎች ሁሉ ከንቱ ናቸው ፤

ኢታምልክዎሙ ወኢትስግዱ ሎሙ፤

አታምልኳቸው አትስገዱላቸው።

፶፩፤ አላ አንትሙሰ አምልኩ አምላከ ልዑለ ፤

እናንተ ግን ልዑል አምላክን አምልኩ እንጅ ፤

ወስግዱ ሎቱ ወትረ ፤

በየጊዜው ለሱ ስገዱለት ፤

ወተሰፈዉ ገጸ ዚአሁ በኵሉ ጊዜ፤

በየጊዜው ሁሉ ገጹ ረድኤቱን አለኝታ ተስፋ አድርጉ ፤

ወግበሩ ፍትሐ ወጽድቀ ወርትዐ በቅድሜሁ ፤

በፊቱ የቀና እውነት ፍርድን ፍረዱ ፤

ከመ ይፍታሕ ላዕሌክሙ፤

በእናንተ ላይ እውነት ፍርድን ይፈርድላችሁ ዘንድ ፤

ወየሀብክሙ ምሕረቶ ፤

ይቅርታውን ይሰጣችሁ ዘንድ፤

ወያውርድ ለክሙ ዝናመ ነግህ ወሠርክ ፤

የማታውንና የጧቱን ዝናብ ያዘንብላችሁ ዘንድ፤ አንድም የግንቦትን የሰኔን የጥቅምትን የኅዳርን ዝናብ ያዘንብላችሁ ዘንድ ፤

ወይባርክ ኵሎ ተግባረክሙ ወኵሎ ዘተገበርክሙ በዲበ ምድር፤

በዚህ ዓለም የደከማችሁበትን ሁሉ አዝመራ ያበዛላችሁ ይባ ርክላችሁ ዘንድ።

፶፬፤ ወይባርክ እክለከ ወማየከ፤

እህልህን ያበረክትልሀል ውሀ ህን ያበዛልሀል ፤

ወይባርክ ዘርዐ ከርሥከ፤

ከባሕርይህ የተከፈለ ልጅህን፤

ወዘርዐ ምድርከ ፤

የሀገርህንም ዘር ያበዛልሀል፤

ወመራዕየ አልሕምቲከ ወመራዕየ አባግዒከ ፤

የላሙን የበጉን መንጋ ይባር ክልሃል ያበዛልሃል ፤

ወትከውን ለበረከት በዲበ ምድር ፤

በዚህ ዓለም ለበረከት ትሆና ለህ።

፶፭፤ ወይፈትዉክሙ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ፤

በዚህ ዓለም ያሉ አሕዛብ ሁሉ ይወዷችኋል ፤

ወይባርኩ ውሉደክሙ በስምየ ከመ ይኩኑ ቡሩካነ ፤

ቡሩካን ይሆኑ ዘንድ በስሜ ልጆቻችሁን ያከብራሉ ፤

በከመ አነ ፤

እኔ እንደተናርኩ ፤

ወወሀቦ ለእስማኤል ወልዱ ወለ ደቂቀ ኬጡራ ሀብተ ፤

ለልጁ እስማኤል ለኬጡራ ልጆች ፈንታ ፈንታቸውን ሰጣቸው ፤

ወፈነዎሙ እምይስሐቅ ወልዱ ፤

ከልጁ ይስሐቅ ለይቶ ሰደዳ ቸው አሰናበታቸው ፤

ወኵሎ ወሀቦ ለይስሐቅ ወልዱ ፤

የቀረውን ገንዘቡን ሁሉ ለልጁ ይስሐቅ ሰጠው ።

፶፬፥ ወሖረ እስማኤል ወልዱ ፤

ልጁ እስማኤል ገንዘቡን ተቀ ብሎ ሄደ ፤

ወውሉደ ኬጡራ ወውሉዶሙ ኅቡረ ፤

የኬጡራ ልጆች የልጅ ልጆ ችም ፈንታቸውን ተቀብለው በአንድነት ሄዱ ፤

ወኀደሩ እምፋርሞን እስከ መባኣ ባቢሎን ወውስተ ኵሉ ምድር እንተ ገጸ ጽባሕ አንጻረ ገዳም ፤

በምድረ በዳው አንጻር ፡ በምሥ ራቅ በኩል ባለው አገር ሁሉ ከፋርስ ጀምሮ እስከ ባቢሎን ባለው መግቢያ ድረስ ኖሩ ፤

ወተደመሩ እሉ ምስለ እሉ ፤

የእስማኤል ልጆች ከኬጡራ ልጆች ጋራ አንድ ሆኑ፤

ወተፀውአ ስሞሙ ዐረብ ወእስማ ኤላውያን ፤

ስማቸውም ዐረብ ነጋዴ እስ ማኤላውያን ተብሎ ተጠራ ።

## ምዕራፍ ፳፩

፩፥ ወበሳድስ ዓመት ዘሳብዕ ሱባዔ ዘዝንቱ ኢዮቤልዩ ፤

በዚህ ኢዮቤልዩ በ፯ተኛው ሱባዔ በሚቆጠር በስድስተ ኛው ዓመት ፤

ፀውዐ አብርሃም ይስሐቅሃ ወልደ ፤

አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ጠርቶ፤

ወአዘዞ እንዘ ይብል አነ ረሣዕኩ ወኢየአምር ዕለተ ሞትየ ፤

እንዲህ ብሎ አዘዘው እኔ አረ ጀሁ የምሞትበትን ቀን አላ ውቅም ፤

እስመ ጸገብኩ መዋዕልየ ፤

ዘመኔን ስልችቻለሁና።

፪፥ ወናሁ አነ ወልደ ፻ወ፸ ወ፭ ዓመት ፤

እንሆ እኔ የመቶ ሰባ አምስት ዘመን ፍጥረት ነኝ ፤

ወበኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ ሀሎኩ እንዘ እዜክሮ ለእግዚአብሔር ፤

ባለ በዘመኔ ሁሉ እግዚአ ብሔርን ሳስበው ኖርኩ ፤

ወእንዘ አኀሥሥ በኵሉ ልብየ ከመ እግበር ፈቃዳቲሁ ለአምላኪየ፤

በፍጹም ልቡናየ የፈጣሪየን ፈቃድ እፈጽም ዘንድ ስፈልግ ኖርኩ ፤

ወከመ አርትዕ ሐዊረ በኵሉ ፍናዊሁ ጣዖተ ጸልዐት ነፍስየ ፤

በቀና ሕጉ ጸንቼ እኖር ዘንድ ሰውነቴ ጣዖቱን ጠላች ፤

ከመ ትዕቀብ ገቢረ ፈቃዱ ለአም ላኪየ ፤

የፈጣሪየን ፈቃድ ማድረግን ትፈጽም ዘንድ ፤

እስመ አምላክ ሕያው ወቅዱስ ውእቱ፤

ሕያው አምላክ ክቡር ንጹሕ አምላክ ነውና ፤

ወምእመን ወጻድቅ ውእቱ እምኵሉ፤

ከሁሉ ይልቅ ቸር የታመነ አምላክ ነውና።

፫፤ ወአልቦ ዓመፃ በኀቤሁ ፤

በሱ ዘንድ ሐሰት የለም ፤

ነሢአ ገጽ ወነሢአ ሕልያን ፤

ለሰው ፊት ማድላት መማለጃ መቀበል የለም ፤

እስመ አምላክ ጻድቅ ውእቱ ፤

ቸር ፈጣሪ ነውና ፤

ወገባሬ ኵነኔ ውእቱ እምኵሎሙ እለ ይትዓደዉ ትእዛዞ ፤

ትእዛዙን ከሚያፈርሱ ሁሉ ፍርዱን ያደርጋልና፤

ወእለ ይሜንኑ ኪዳኖ ፤

ሕጉን የሚንቁ ሰዎችን ሁሉ ይፈርድባቸዋል።

፬፤ ወአንተኒ ኦወልድየ ዕቀብ ትእዛዞ ወሥርዐቶ ወኵነኔሁ ፤

ልጄ! አንተም ሕጉን ሥርዓ ቱን ፍርዱን ጠብቅ ፤

ወኢትሑር ድኅሬሆሙ ለርኩሳን፤

ርኩሳን የሚሆኑ ጣዖታትን ተከትለህ አትሂድ ፤

ወድኅሬሆሙ ለግልፎ ፤

የተቀረጸ ጣዖትን ለመከተል አትሂድ ፤

ወድኅሬሆሙ ለስብኮ ፤

ተመትቶ የተሠራ ጣዖትን በመከተል አትሂድ ፤

ወኢትብላዕ ወኢምተኒ ደመ ዘአ ርዌ ወዘእንስሳ ፤

የእንስሳን የአራዊትን ደም ምንም አትብላ ፤

ወዘኵሉ ዖፍ ዘይሠርር ውስተ ሰማይ ፤

በሰማይ የሚበር የወፉን ሁሉ ደም አትብላ።

፳፤ ወለእመ ሐረድከ ሕርድ ለጽ ንሐሐ ሰላም ዘይሠጠው ፤

ብታርድም ወደ የሚቀበለውን አንተን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርግ መሥዋዕ ትን ሠዋ ፤

ሕርድ ወደሞሙ ትክው ውስተ ምሥዋዕ ፤

አርደህ የመሥዋዕቱን ብዕዓት ደም ከመሠዊያው በታች አፍ ስሰው ፤

ወኵሎ ስብሐ ጽንሐሕ ታዐርግ ውስተ ምሥዋዕ ምስለ ስንዳሌ ፤

የሚጤሰውን ስቡን ልጦ ጉርዶ ከወጣው ስንዴ ጋራ ወደ መሠዊያው አቅርብ ፤

ወመሥዋዕተ ልውስ በቅብዕ ምስለ ሞጻሕቱ ታዐርግ ኵሎ ኅቡረ ዲበ ምሥዋዕ ፤

በዘይት የታሸውን መሥዋዕ ቱን ከወይኑ ጋራ አንድ አድ ርገህ ወደመሠዊያው አው ጣው ፤

ጽንሐሐ መዓዛ ሠናይ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው በጎ መዓዛ ያለውን መሥዋ ዕት አቅርብ ፤

በከመ ስብሐ መሥዋዕተ መድኃኒት ታነብር ዲበ እሳት ዘዲበ መሥዋ ዕት በከመ ስብሕ ዘዲበ ከርሥ ፤

ድኅነት እንደሚደረግባት መሥ ዋዕት በሆድ ውስጥ ያለውን ስብ በመሠዊያው ባለ በእሳቱ ላይ አኑር።

፳፩፤ ወኵሎ ስብሐ ዘዲበ ንዋየ ውስጥ ፤

በሆድ ዕቃው ውስጥ ሁሉ ያለውን ስብ ፤

ወ፪ተ ኵልያተ ፤

ሁለቱን ኩላሊቶች

ወኵሎ ስብሐ ዘዲቤሆሙ ፤

በነዚያ ላይ ያለውን ስቡን ሁሉ ፤

ወዘዲበ መናቅዕ፤

በላቱ ላይ ያለውን ስቡን ፤

ወከብዶ ምስለ ኵልያት ጥብሉለ ፤

ግልገል ጉበቱን ከኵላሊቶቹ ጋር እንደተጠቀለለ።

፯፤ ወታዐርግ ዘንተ ኵሎ ለመዓዛ ሠናይ ፤

እግዚአብሔር በጎ መዓዛ አድ ርጎ ሊቀበለው ይህንን ሁሉ አቅርብ ፤

ወዘይሠጠው ቅድመ እግዚአብሔር ምስለ መሥዋዕቱ ወሞዓሕቱ ፤

ከመሥዋዕቱ ከወይኑ ጋር እግ ዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው፤

ለመዓዛ ሠናይ ኅብስተ ጽንሐሕ ፤

ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ሊሆን ኅብስቱን ስቡን አቅርብ፤

ወሥጋሁ ብላዕ በይእቲ ዕለት ወበሣኒታ ፤

ሥጋውን በዚች ቀን በማግስ ቱም ብላ።

፰፤ ወኢይዕርብ ላዕሌሃ ፀሐይ ዘእመ ሣኒታ እስከ ሶበ ይትበላዕ ፤

በማግስቱ ይህ ሥጋ እስኪበላ ድረስ ፀሐይ አይግባ ፤

ወኢይትርፍ ለዕለት ሣልስት እስመ ኢይሠጠዎ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር አይቀበለውምና ለሦስተኛው ቀን አይትረፍ ፤

እስመ ኢኮነ ኅሩየ ወኢይትበላዕ እንከ ፤

የማይገባ ስለሆነ ከዚያ በኋላ አይበላ ፤

ወኵሎሙ እለ ይበልዕዎ ኃጢአተ ሎሙ ይነሥኡ ፤

የበሉት ሰዎች ሁሉ የኃጢአ ታቸውን ፍዳ ይቀበላሉ።

፱፤ እስመ ከመዝ ረከብኩ ጽሑፈ ውስተ መጽሐፈ አበውየ ቀደምት ውስተ ነገረ ሄኖክ ወውስተ ነገረ ኖኅ ፤

የቀደሙ አባቶቼ ሄኖክ ኖኅ በጻ ፉት መጽሐፍ እንዲህ የሚል ጽሑፍ አግኝቸአለሁና፤

ወውስተ ኵሉ መሥዋዕትከ ትወዲ ዔወ ፤

በመሥዋዕትህ ሁሉ ጨው ጨምርበት ፤

ወኢይጸራእ ኪዳን ዔው ውስተ ኵሉ መሥዋዕቲከ ቅድመ እግዚ አብሔር ፤

በእግዚአብሔር ፊት በሚሠ ዋው በመሠዊያው በሚቀር በው ሁሉ የጨው ሥርዐት አይቅር ።

፲፤ ወተዐቀብ በዕፀወ መሥዋዕት፤

መሥዋዕት በሚሠዋባቸው እን ጨቶች ተጠበቅ ፤

ከመ ታብዕ ዕፀወ ዲበ ምሥዋዕ ዘንተ ከመ ፤

እነዚህኑ እንጨቶች ብቻ ወደ መሠዊያው ታቀርብ ዘንድ ፤

ቂጽርሶን፤

ሰኖባር የሚባል ዕንጨት ነው፤

ወዲፍራን፤

ቀረጥ፤

ወሠጋድ፤

ሰገድ፤

ወሰጥራቢሎን ፤

ሽነት፤

ወጲጦን ፤

ወይራ ፤

ወቄድሮን ፤

ዋንዛ ፤

ወጥራቴ ፤

ዶቅማ ፤

ወቲናክ ፤

ጠዶ ፤

ወዕፀ ዘይት ፤

በቁሙ ዕፀ ዘይት ፤

መርሳኒ ፤

ብርስነት ፤

ወጣፍን ፤

ጥድ ፤

ወቄዳር፤

ቀጋ ፤

ዘስሙ አርበቅ ፤

ስሙ አርበቅ የሚባል ቀጋ፤

ወቢሶም ፤

ሾላ ናቸው ።

፲፩፤ ወእምእሉ ዕፀው አንብር ታሕተ ጽንሐሕ ዲበ ምሥዋዕ ፤

ከነዚህ እንጨቶች ወገን የሚ ሆነውን ከመሠዊያው በላይ

ከስቡ በታች አኑር ፤

ምኩረ ረዓዮሙ ፤

ምጡን ረዓዮሙ ሲል ነው፤ መልካቸው የበቃ በነዚህ ብቻ ሠዋ ፤ ለክተህ መጥነህ አኑ ራቸው ፤

ወኢታንብር ኵሎ ዕፀ ንቁአ፤

የነቀዘውንዕንጨት አታድርግ፤

ወፌዋ ዕፀወ ፤

የበሰበሰውን እንጨት ፤

ወዕፀወ ጽኑአነ ፤

አላ ያለበት ነው፤ ለጋ ለጋውን ዕንጨት ፤

ወሠናያነ ዘአልቦ ምንትኒ ነውር ፍጹመ ፤

የተለቀመውን ነውር ነቀፋ የሌ ለውን ያምጡ ፤

ወሐዲሰ ተክለ ፤

አዲሱን ዕንጨት አድርግ እንጂ።

፲፪፤ ወኢታንብር ዕፀ ብሉየ ፤

አሮጌውን ዕንጨት አታቅርብ፤

እስመ ወጽአ መዓዛሁ ፤

መዓዛው ተለይቶታልና ፤

እስመ ኮነ እንከ ዘአልቦ መዓዛ ላዕሌሁ ከመ ቀዳሚ ፤

መጀመሪያ እንደነገር ኩህ ምንም ምን መዓዛ የለውምና፤

ዘእንበለ እሉ ዕፀው አልቦ ዘታነብር ባዕድ ፤

ምንም ምን አይሁን ከነገር ኩህ ዕንጨት በቀር ለመሥ ዋዕት የምታቀርበው ዕንጨት አይኑር ፤

እስመ መዓዛሁ ፍሉጥ ፤

መዓዛው የተለየ ነውና ፤ ወየዐርግ ጼና መዓዛሁ እኩይ ውስተ ሰማይ ፤

መዓዛው ከእግዚአብሔር ፊት ይደርሳል፤ ከነዚህ እንጨቶች በቀር ሌላ እንጨት አታቅርብ፤

ወኢይሰጠዎ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር አይቀበለውምና።

፲፫፤ ዕቀብ ወልድየ ዘንተ ትእዛዘ ፤

ልጄ የነገርኩህን ትእዛዝ ጠብቅ፤

ወግበር ሠናየ ግብረ ከመ ታርትዕ በኵሉ ግብርከ ፤

ልጄ ሥራህን ሁሉ የቀና ታደ
ርግ ዘንድ ያዘዝሁህን ሁሉ
ጠብቅ ፤

ወበኩሉ ጊዜ ኩን ንጹሐ በሥጋከ ፤

በየጊዜው ሁሉ ሰውነትህን
ንጹሕ አድርግ ፤

ወሕፅብ በማይ ዘእንበለ ትሑር
ለአዕርጎ ውስተ ምሥዋዕ ፤

መሥዋዕቱን ለማሳረግ ወደ
መሠዊያው ሳትወጣ ሰውነት
ህን በውሀ እጠብ ፤

ወሕጽብ እደዊከ ወእገሪከ ዘእንበለ
ትቅረብ ውስተ ምሥዋዕ ፤

ወደ መሠዊያው ሳትቀርብ አስ
ቀድመህ እጅህን እግርህን
ታጠብ።

፲፬፤ ወሶበ ፈጸምከ አዕርጎ መሥ
ዋዕት ግባዕ ወተሐፀብ እደዊከ
ወእገሪከ ፤

መሥዋዕቱን ፈጽመህ ካሳረ
ግህ በኋላ እጅህን እግርህን
ታጠብ ፤

ወኢያስተርኢ በዲቤክሙ ኩሉ
ደም ወውስተ አልባሲክሙ ፤

በሰውነታችሁም በልብሳችሁም
ላይ ምንም ምን ደም አይታይ።

፲፭፤ ተዐቀብ ወልድየ በደም ፤

ልጄ ባደረው ደም እንዳትሠዋ
ተጠንቀቅ፤ ሐተታ ሽክላ ቢሉት
ይስበሩት ብረት ቢሉት ይሰን
ግሉት ይወልውሉት ይላልና፤

ወተአቀብ ጥቀ ወድፍኖ ለደም
ውስተ ምድር ፤

ፈጽመህ ተጠበቅ ደም ፈሶ
ብታገኝ አፈር አልበሰው ፤

ወኢትብልዑ እንከ ደመ ፤

እንደ አሕዛብ ቆልታችሁ ቀቅ
ላችሁ ደምን አትብሉ ፤

እስመ ደም ነፍስ ይእቲ ፤

ደም ነፍስ ናትና፤

ሐተታ እንደ ኦሪት ፤

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕ ፲፯
ከቁጥር ፲፫-፲፬ ፤

ወኢትብላዕ ምንተኒ ደመ ፤

ምንም ቢሆን ደም አትብላ
ወኢትንሣእ ሕልያነ ዲበ ኩሉ
ደመ ሰብእ ፤

በማይገባ ሐሰት መስክረህ በሐሰት ፈርደህ የሰውን ደም ለማፍሰስ መማለጃ አትቀበል፤

ከመ ኢይትከዐው በከ ዘእንበለ ኵነኔ፤

በእውነት ሳትፈርድ የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ ፤

እስመ ደም ውእቱ ዘይትከዓው በከ የኃጥኣ ለምድር ፤

ያጠፍኣ ሲል ነው፤ በማይገባ የፈሰሰ የሰው ደም ምድርን ያጠፋታልና ፤

ወደም ኢትክል ነጺሐ እምደመ ሰብእ ዘእንበለ በደም ዘከዓዎ ፤

የገደለውን ቢገድሉ ነው እንጅ ያለዚያ ደም አይነፃም።

፲፯፤ ወኢትንሣእ ኅልያነ ወአምኃ በደመ ሰብእ ፤

በሰው ደም መማለጃ እጅ መንሻ አትቀበል ፤

ደመ በደም ይሠጠው ቅድመ እግ ዚአብሔር ልዑል ፤

በልዑል እግዚአብሔር ፊት በፈ ሰሰው ደም ፍዳ ደምን ብታፈስ ደም በደም ይመለሳል ፤

ወይከውን ዓቃቢሁ ለሠናይ ፤

መልአከ ዑቃቤውም ለበጎ ነገር ይጠብቀዋል ፤

ወከመ ትትዐቀብ እምኵሉ እኩይ ፤

ከመከራው ሁሉ ትጠበቅ ዘንድ፤

ወከመ ያድኅንከ እምኵሉ ሞት ፤

ከሞት ከመከራ ያድንኅ ዘንድ መማለጃውን እጅ መንሻውን አትቀበል።

፲፯፤ እሬኢ አነ ወልድየ ኵሎ ግብረ ዕጓለ እመሕያው ከመ ኃጢአት ወእከይ ፤

ልጄ ! የሰው ሁሉ ሥራው ክፋት ኃጢአት እንደሆነ አያ ለሁ አውቃለሁ ፤

ወኵሉ ግብሮሙ ርኩስ ወምናኔ ወግማኔ ፤

ሥራቸው ሁሉ ፈጽሞ የተ ጠላ የተናቀ እንደሆነ አወቅሁ፤

ወአልቦ ጽድቅ ምስሌሆሙ ፤

ከነሳቸው ጋራ እውነት ነገር ምግባር ትሩፋት የለም።

፲፰፤ ተዐቀብ ወኢትሑር ውስተ ፍኖቶሙ ፤

እነሳቸው በኼዱበት ጎዳና

እንዳትሄድ ተጠበቅ ማለት እነዚያ የሠሩትን ሥራ እን ዳትሠራ ተጠበቅ ሲል ነው ፣

ወኢትኪድ ውስተ አሠሮሙ ፣ ፍለጋቸውን ለመሻት እንዳት ሔድ ተጠበቅ ፤

ወኢትስሐት ስሕተተ እስከ ለሞት ቅድመ እምላክ ልዑል ፤

በልዑል እግዚአብሔር ፊት ለሞት የሚያበቃ በደል እንዳ ትበድል ተጠበቅ ፡

ወየኀብእ ገጾ እምኔከ ፣

እንዲህ ያደረግህ እንደሆነ ገጸ ረድኤቱን ከአንተ ይሠውራል፣

ወያገብእከ ውስተ እደ አበሳከ ፡

ወደሠራኸው ኃጢአት ፍዳ ይመልስሃል ፣

ወይሤርወከ እምነ ምድር ፣

ከዚህ ዓለም ነቃቅሎ ያጠፋ ሃል ፣

ወዘርዓከኒ እምታሕተ ሰማይ ፣

ልጅህንም የልጅህንም ልጅ ከዚህ ዓለም ያጠፋል ፣

ወይትኀጎል ስምከ ወዘርዕከ እም ኵሉ ምድር ፣

ስምህም ልጅህም ከዚህ ዓለም ይጠፋል።

፲፱፣ ወተገኀሥ እምኵሉ ምግባሪሆሙ ፣

ክፉዎች ሰዎች ከሚሠሩት ሥራ ራቅ ፤

ወእምኵሉ ርኵሶሙ ፤

ከሚያመልኩትም ጣዖት ራቅ፣

ወተዐቀብ ዑቃቤ ዘእምላክ ልዑል፤

የእግዚአብሔርን ሕግ ትጠ ብቅ ዘንድ ከገቢረ ኃጢአት ከአምልኮ ጣዖት ተጠበቅ ፣

ወግበር ፈቃዳቲሁ ፣

ፈቃዱንም ፈጽም፣

ወታረትዕ በኵሉ ፣

ሥራህን ሁሉ የቀና አድርግ

ወይባርክከ በኵሉ ምግባሪከ ፣

በምትሠራው ሥራ ሁሉ እግ ዚአብሔር ያከብርሃል ፣

ወያነሥእ እምኔከ ተክለ ጽድቅ ፣

ከአንተ ወገን ሕግ የሚጠብቅ ልጅ ያስነሣል ፣

በኵሉ ምድር ወበኵሉ ትውልደ ምድር ፣

ለልጅ ልጅ ዘመን በዚህ ዓለም ሁሉ እውነተኛ ልጅ ያስነሣል፣

ወይትአመር ስምየ ወስምከ በመት ሕተ ሰማይ በኵሉ መዋዕል፣

በዘመኑ ሁሉ በሰማይ በታች ባለ በዚህ ዓለም የእኔም ያን ተም ስም ይጠራል ፡፡

፴፣ ወሑር ወልድየ በሰላም ፣

ልጄ ! በዘመኑ ሁሉ በተድላ በደስታ ኑር ፣

ያጽንዓከ አምላክ ልዑል አምላኪየ ወአምላክከ ለገቢረ ፈቃዳቲሁ ፣

የኔም ያንተም ገናና ፈጣሪ የሆነ ፈቃዱን ለመፈጸም አጽ ንቶ ያኖርኃል ፣

ወይባርክ ኵሎ ዘርዐከ ወተረፈ ዘርዕከ ለትውልደ ትውልድ ዘለዓ ለም በኵሉ በረከተ ጽድቅ ፣

ልጅህን የልጅ ልጅህን ፈጽሞ ለዘለዓለም ያከብራል ፣

ከመ ትኩን ለበረከት በኵሉ ምድር፣

ባገኘሀት በዓለም ሁሉ ለዘለ ዓለም የከበርህ ትሆን ዘንድ ፣

ወወጽአ እምኀቤሁ እንዘ ይትፌ ሣሕ ይስሐቅ ፣

ይስሐቅም ደስ እያለው ከአ ባቱ ዘንድ ወጣ፡፡

## ምዕራፍ ፲፮

፩፣ ወኮነ በቀዳሚ ሱባዔ በ፵፬ ወ፬ቱ ኢዮቤልዩ በካልዕ ዓመቱ ፣

በመጀመርያው ሱባዔ በ፵፬ተ ኛው ኢዮቤልዩ በሁለተኛው ዓመት ፣

ወውእቱ ዓመት በዘሞተ አብርሃም፣

ይኸውም አብርሃም የሞተበት ዘመን ነው ፣

መጽኡ ይስሐቅ ወእስማኤል እምዓ ዘቅተ መሐላ ፣

ይስሐቅና እስማኤል ከቤርሳ ቤህ መጡ ፣

ከመ ይግበሩ በዓለ ሱባዔ ዛቲ በዓል በቀዳሚ ማዕረር ኀበ አብር ሃም አቡሆሙ ፣

በሱባዔ የምትከበር ይህችን በዓል ከማክበር አስቀድሞ ያከ ብሩ ዘንድ ወደ አባታቸው አብርሃም መጡ፡፡

፪፣ ወተፈሥሐ አብርሃም እስመ ፪ሆሙ ደቂቁ መጽኡ ኀቤሁ ፣

አብርሃምም ሁለቱ ልጆቹ ስለ